
# የታዳጊዎች የህግ ሥርዓት የቤተሰብ መምሪያ መጽሐፍ

የኪንግ ካውንቲን ታዳጊ የሕግ ስርዓት
መረዳትና መመርመር




ዜሮ የወጣቶች እስር
King County

የ 2020
እትም

# የርዕስ ማውጫ


| ርዕስ | የገጽ ቁጥር |
|---|---|
| ዜሮ የወጣቶች እስር ቤት ማቆያ ታሪክ ካርታ (ምስል) | 3 |
| መግቢያ | 4 |
| ሰነድ አልባ ብሆንስ? | 5 |
| እንግሊዝኛ ባልናገርስ? | 5 |
| በታዳጊዎች የሕግ ሥርዓት ውስጥ ያሉ ባለሙያዎች (ምስል) | 6 |
| የታዳጊዎች የሕግ ስርዓት መምሪያዎች እና ባለሙያዎች | 7 |
| የፖሊስ መምሪያዎች | 7 |
| የ King County ዓቃቤ ሕግ ቢሮ | 7 |
| የኪንግ ካውንቲ የሕዝብ መከላከያ መምሪያ | 7 |
| የኪንግ ካውንቲ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የታዳጊዎች ክፍል | 8 |
| ልጅዎ በአመክሮ ጊዜ ላይ ሲሆን | 8 |
| የአመክሮ ጊዜ መረጃ | 8 |
| የኪንግ ካውንቲ የአዋቂዎች እና የታዳጊዎች ማቆያ መምሪያ | 9 |
| ልጅዎ ሲታሰር/በቁጥጥር ውስጥ ሲውል | 9 |
| ልጅዎ በታዳጊዎች እስር ቤት ሲደርስ ምን ይሆናል | 9 |
| ልጅዎ በቤተሰብ አመፅ/ጥቃት ምክንያት ከታሰረ FIRS (ኤፍ.አይ.አር.ኤስ) | 11 |
| ልጅዎ በእስር ላይ ከሆነ ምን ማድረግ ይችላሉ | 11 |
| ለልጅዎ ጥብቅና መቆም | 12 |
| በታዳጊዎች እስር ቤት ምን ይከሰታል? | 13-15 |
| ልጄ በደል ወይም ቸልተኝነትን ሪፖርት ካደረገስ? | 15 |
| የፍርድ ቤቱ ሂደት | 15-26 |
| የታዳጊ ፍ/ቤቶችን ለመጎብኘት ጠቃሚ ምክሮች | 15 |
| የፍርድ ቤት ችሎቶች | 16 |
| የፍርድ ቤቱ ሂደት (ምስል) | 16-18 |
| የመጀመሪያ ችሎት | 19 |
| ተጨማሪ ችሎቶች | 19-21 |
| ብዙም ያልተለመዱ ችሎቶች (ምስል) | 22 |
| ብዝሃነት | 23 |
| ደጋፊ የፍርድ ቤት ፕሮግራሞች እና ጥምረቶች | 23-27 |
| የባህርይ ጤና ምላሽ | 24 |
| የአመፅ መተኪያ ሥልጠና (ART) | 24 |
| በስጋት ላይ ያሉ ወጣቶች (ኤ.አር.አይ)፣ ለአገልግሎት የሚያስፈልጋቸው ሕፃናት (ሲ.ኤች. አይ.ኤን)፣ እና ያለፍቃድ ከት/ቤት የመቅረት ፕሮግራሞች | 24-25 |
| የታዳጊዎች የፍትህ ምዘና ቡድን (ጄ.ጄ.ኤ.ቲ) | 25 |
| የበላይ ፍርድ ቤት የልጆች እና የቤተሰብ መርጃ/ሀብት ማዕከል | 26 |
| እስርን የማስጠበቅ አማራጮች፡- የኤሌክትሮኒክ የቤት ቁጥጥር እና የቡድን እንክብካቤ | 27 |
| መዝገቦችን **መመለስ** | 27 |
| ብዙ ጊዜ የሚያገለግሉ ቃላት | 29-31 |
| ምህጻረ-ቃላት | 32 |
| የማህበረሰብ ሀብቶች እና አገልግሎቶች | 33-39 |
| እውቅናዎች | 39 |

ይህንን መመሪያ ለመረዳት እገዛ ከፈለጉ እባክዎ ከማንኛውም የኪንግ ካውንቲ ታዳጊ የሕግ ሥርዓት ባለሙያ ጋር ይመርምሩ ወይም zydinfo@kingcounty.govን ያነጋግሩ። ይህ መመሪያ በአማርኛ፣ በማርሻሊዝ፣ በሩስያኛ፣ በሶማሊኛ፣ በስፓኒሽ፣ በትግርኛ እና በቬትናምኛ ቋንቋዎች ይገኛል።

# መግቢያ

አንድ ልጅ በታዳጊ የሕግ ሥርዓት ውስጥ በሚሳተፍበት ጊዜ፣ ወደዚያ ያደረሳቸውን ክስተቶች ለመቀየር ቤተሰቦች ብዙ ጊዜ እና ጉልበት ካሳለፉ በኋላ አብዛኛውን ጊዜ ይደክማሉ። እንደ ተንከባካቢ፣ እርስዎ በትምህርት ቤቶች እና በምክር አገልግሎት ድጋፍን ፈልገው ይሆናል። አገልግሎቶችን ለማግኘት እንቅፋቶች ስላጋጠምዎት ተበሳጭተው ይሆናል። እርዳታ ለማግኘት የተደረገው ሙከራ ምንም ይሁን ምን፣ የቤተሰብ አባላት ብዙውን ጊዜ ለልጃቸው ባህሪ እራሳቸውን ይወቅሳሉ።

ለልጅዎ ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢ መፍጠር የእርስዎ ኃላፊነት ብቻ አይደለም። ልጆች እንዲበለፅጉ የሚያስችል ሁኔታን ማመቻቸት የመላው ማህበረሰብ ኃላፊነት ነው። ይህንን ዑደት/ዙረት ለማቋረጥ በሕጋዊ ሥርዓት ውስጥ ያሉ ሰዎች ከማንኛውም ሀብቶች፣ ድጋፎች እና አገልግሎቶች ጋር ያገናኙዎታል። ከህግ ስርዓት ጋር መያያዝ ከባድ ጉዳይ ነው እናም ልጅዎ በወንጀል ከተከሰሰ፣ ዘላቂ መዘዞችን ሊያስከትል ይችላል።

ኪንግ ካውንቲ ልጆች በሚፈልጉበት ጊዜ የሚፈልጉትን እርዳታ እንዲያገኙ የተጠናከረ የማህበረሰብ ድጋፎችን ለመገንባት ጠንክሮ እየሰራ ያለው ለዚህ ነው። እነዚህ የህብረተሰብ ድጋፎች ደህንነቱ የተጠበቀ እስር ወይም ተጨማሪ የህግ ስርዓት ተሳትፎን የሚያስወግዱ መፍትሄዎችን ይፈልጋሉ። በአስርተ ዓመታት የተደረጉ ምርምሮች እንደሚያሳዩት ወጣቶችን ወደ እስር ቤት ማስገባት የህዝባዊ ደህንነትን አያበረታታም እናም ይልቁን ወጣቶችን፣ ቤተሰቦቻቸውን፣ እና ማህበረሰቦቻቸውን ይጎዳል። ልጆች፣ ቤተሰቦች፣ እና ማህበረሰቦች ደስተኛ፣ ጤናማ፣ ደህና እና የበለፀጉ እንዲሆኑ የተሻለ ማድረግ እንችላለን እና ደግሞም ማድረግ አለብን።

እስከዚያው ድረስ፣ እንደ ወላጅ፣ ልጅዎ ከታሰረ በኋላ ምን ማድረግ እንዳለብዎ ለማወቅ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ነዎት። ስለ ልጅዎ እና ስለ ደህንነታቸው ብዙ ጥያቄዎች ሊኖርዎት ይችላል። ልጄ ደህና ነው? ልጄ አሁን የት ነው ያለው? ልጄን ወደ ቤት መቼ ማምጣት እችላለሁ? መቼ ማየት ወይም ማናገር እችላለሁ? ምን ማድረግ አለብኝ? ማንን ማመን እችላለሁ? ቀጥሎ ምን ይከሰታል?

ይህ መመሪያ የተሰራው COVID-19 ን ለመከላከል ማህበራዊ ርቀትን የሚያለማምዱ እርምጃዎች ሲወሰዱ ነው። በአገልግሎቶች፣ በፍርድ ቤት ችሎቶች፣ እና በታዳጊዎች እስር ጉብኝት ላይ የማይንፀባረቁ ልዩነቶች ሊኖሩ ይችላሉ።

**ይህ መመሪያ የተዘጋጀው ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት በሚፈልጉ ወላጆች እና በቤተሰብ ተሟጋቾች ነው። ይህ መመሪያ ስለ ታዳጊዎች የሕግ ሥርዓት ጥልቅ ማብራሪያ እንዲሆን የታሰበ አይደለም። ይልቁንም፣ ይህ መመሪያ በስርዓቱ ውስጥ ያለዎትን ሚና በተሻለ እንዲገነዘቡ እና እርስዎ ወይም ልጅዎ ከሚፈልጓቸው ማናቸውም ድጋፎች ጋር ለመገናኘት ይረዳዎታል ብለን ተስፋ እናደርጋለን።**

# ሰነድ አልባ ብሆንስ?

ኪንግ ካውንቲ የኢሚግሬሽን ሁኔታቸው ምንም ይሁን ምን ሁሉንም ሰው ለመቀበል እና ለማገልገል ቁርጠኛ ነው። መሰደድ በጣም ከባድ ተሞክሮ ነው እናም በአዲስ ባህል ውስጥ ልጆችን ማሳደግ ፈታኝነቱን ይጨምራል። በኪንግ ካውንቲ ውስጥ ከሚገኙት የመንግሥት መምሪያዎች መካከል አንዳቸውም ስለ ኢሚግሬሽን ሁኔታ የሚጠይቁ አይደሉም። የአከባቢ ፖሊስ አንድ ሰው በቁጥጥር ስር እየዋለ እያለ ስለ የኢሚግሬሽን ሁኔታ አይጠይቅም።ይህ መረጃ አይተላለፍም፣ አይሰበሰብም ወይም ጥቅም ላይ በሚውሉ ማናቸውም የውሂብ ጎት/ዳታቤዞች ውስጥ አይቀመጥም። ልጅዎ ሰነድ አልባ ከሆነ፣ ከታሰሩ ከሀገር እንዲባረሩ አይደረግም። በኪንግ ካውንቲ የታዳጊዎች የሕግ ሥርዓት ውስጥ ያሉ ባለሙያዎች ስደተኛ ቤተሰቦች በተጠየቁት መሠረት ከተወሰኑ ሀብቶች ጋር ለማገናኘት ሀብቶች አሏቸው። ይህንን እርዳታ ለመስጠት የቤተሰቦችን የሰነድ ሁኔታ ማወቅ አስፈላጊ አይደለም።

[ለ King County Immigrant and Refugee Program (የኪንግ ካውንቲ ስደተኛ እና የኢሚግራንቶች ፕሮግራም)](#) እዚህ ጠቅ ያድርጉ ወይም ለ King County Office of Equity and Social Justice (ኪንግ ካውንቲ የእኩልነት እና ማህበራዊ ፍትህ ቢሮ) በ (206) 477-7525 ወይም (206) 263-3434 ይደውሉ።

# እንግሊዝኛ ባልናገርስ?

ሁሉም ሰዎች፣ ከብሔራዊ መገኛቸው/ምንጫቸው እና የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታቸው ምንም ይሁን ምን በግዛት የፍርድ ሂደት እና ፕሮግራሞች ውስጥ ትርጉም ባለው ሁኔታ የመሳተፍ መብት አላቸው። የፍርድ ቤት ጉዳዮች ብዙውን ጊዜ ልዩ ቃላትን የሚጠይቁ በከፍተኛ ደረጃ የተዋቀሩ፣ አስጨናቂ ልምዶች ናቸው። ውጤታማ የቋንቋ አገልግሎቶችን ለመስጠት ጥንቃቄ የተሞላበት ትኩረት ሳይኖር ብዙ ሰዎች በፍርድ ሂደቶች ውስጥ ሙሉ በሙሉ የመሳተፍ ችሎታ ላይ ኢ-ፍትሃዊ እና ህገ-መንግስታዊ ያልሆነ ሸክሞችን የሚጭን የፍርድ ሂደት ያጋጥማቸዋል።

ሁሉም ከኪንግ ካውንቲ የመጡ ሰራተኞች ለአካል ስብሰባዎች እና ለስልክ ጥሪዎች የስልክ ትርጉም አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ። ስምዎን፣ የስልክ ቁጥርዎን፣ እና የሚናገሩትን ቋንቋ ስም ማሳወቅ ከቻሉ፣ የኪንግ ካውንቲ ሰራተኛ ከአስተርጓሚ ጋር መልሰ ሊደውልዎት ይችላል። እንግሊዝኛ ተናጋሪ ከሆኑ ግን በአስተርጓሚ መናገር የበለጠ ምቾት ከሰጥዎት እባክዎን ለማንኛውም አስተርጓሚ ይጠይቁ። ማንኛውንም ግራ መጋባት ለማስወገድ እና ሂደቱን ለማሻሻል ስለ መረጃው ቀለል ማለትዎ እና ግልጽ መሆንዎ የተሻለ ነው።


አስተርጓሚዎች ውይይቱን ብቻ በቀጥታ ሊተረጉሙ ይችላሉ፣ እና **ድጋፍ** ወይም ምክር መስጠት አይችሉም እንዲሁም አይገባም።

### በፍርድ ቤት ለሚደረጉ ስብሰባዎች ትርጓሜ

ስለ አስተርጓሚ መኖር/ተደራሽነት ከጠበቃዎ ወይም ከእርስዎ Juvenile Probation Counselor (JPC፣ የታዳጊዎች አመክሮ አማካሪ) ማጣራት ይችላሉ። እንደሚያስፈልገዎት ከነገሯቸው ለሁሉም የፍርድ ቤት ኹነቶችዎ ነፃ አስተርጓሚ መኖራቸውን የፍርድ ቤት ሰራተኞች ማረጋገጥ አለባቸው። **የትርጓሜ አገልግሎቱን በቀጥታ ማነጋገር አያስፈልግዎትም፣ ግን ጥያቄዎች ካሉዎት ማነጋገር ይችላሉ፦** Interpreters for Court Matters (የፍርድ ቤት ጉዳዮች አስተርጓሚዎች) (206) 477-1415 scinterp@kingcounty.gov.

*ከአፍጋኒ እስከ ዙሉ፣ Superior Court's Office of Interpreter Services (OIS፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የአስተርጓሚ አገልግሎቶች ቢሮ) እንግሊዝኛ ተናጋሪዎች ያልሆኑትን በፍርድ ቤት ጉዳዮች ለማገዝ ከ 160 ለሚበልጡ ቋንቋዎች አስተርጓሚዎችን ያገኛል። የትርጓሜ አገልግሎቶች ለሁሉም የፍርድ ቤት ኹነቶች ያለምንም ወጪ ይሰጣሉ።*

# በታዳጊዎች የሕግ ሥርዓት ውስጥ ያሉ ባለሙያዎች



# የታዳጊዎች የሕግ ስርዓት መምሪያዎች እና ባለሙያዎች

የታዳጊዎች የሕግ ስርዓት በብዙ የኪንግ ካውንቲ መምሪያዎች እና ከማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር ባላው አጋርነት የተዋቀረ/የተሰራ ነው። ልጅዎ ላይ ተጽዕኖ ያላቸው ውሳኔዎች በሂደቱ የተለያዩ በታዎች ላይ በተለያዩ ሰዎች ይወሰዳሉ። ምን ዓይነት ውሳኔዎች እየተደረጉ እንደሆኑ እና ውሳኔውን መወሰን ስልጣን ያለው ማን እንደሆነ ዘወትር ማወቅ አለብዎት። ስለልጅዎ ሁኔታ የበለጠ ባወቁ መጠን እነሱን በተሻለ ሊደግፏቸው ይችላሉ። ከልጅዎ ጋር አብረው የሚሰሩ ሰዎችን ስም፣ የስራ ድርሻ፣ የቢሮ ስም እና የስልክ ቁጥር መፃፍዎን ያረጋግጡ። እነዚህን ሁሉ መረጃዎች በአንድ ላይ የሚይዙበት አንድ ማስታወሻ ደብተር ቢኖርዎት ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

ከዚህ በታች ካሉት መግለጫዎች በተጨማሪ፣ እያንዳንዳቸው መምሪያዎች ድረ-ገጽ አላቸው። ስለ ስራዎቻቸው፣ ስለ ሚናዎቻቸው እና ስለ አገልግሎቶቻቸው የበለጠ ዝርዝር መግለጫዎችን ለማግኘት እባክዎ እነዚያን ድረ-ገጾች ይጎብኙ እና እያንዳንዱን ክፍል በቀጥታ ያነጋግሩ።

## የፖሊስ መምሪያዎች

ልጅዎ ከፖሊስ መኮንን ጋር ግንኙነት ካለው፣ ይህ መኮንን ለ King County Sheriff's Office (ኪንግ ካውንቲ የፖሊስ መኮንን ቢሮ)፣ ወይም ለአከባቢው ከተማ የፖሊስ መምሪያ ሊሠራ ይችላል። አንድ የፖሊስ መኮንን ለአንድ ጉዳይ ምላሽ ሲሰጥ የሁኔታውን ደህንነት እና ወንጀል መፈጸሙን ወይም አለመፈጸሙን ይገመግማል። ምርመራ ካደረጉ በኋላ፣ ወጣቱ በወንጀል ውስጥ የተሳተፈ መሆኑን ሊወስኑ ይችላሉ። ልጅን በቁጥጥር ስር ለማዋል እና ደህንነት ባለው እስር እንዲጠብቁ ወይም የ **ሪፈራል** (ፖሊስ ሪፖርት) ለ **Prosecuting Attorney's Office (PAO፣ ዐቃቤ ሕግ ቢሮ)** ለማቅረብ ሊወስኑ ይችላሉ።

## የኪንግ ካውንቲ ዓቃቤ ሕግ ቢሮ

1211 East Alder St. Seattle, Washington 98122-5553
የቢሮ ሰዓታት፡- ከሰኞ – ዓርብ ከ 8:30am እስከ 4:30pm
(206) 477-3044

በኪንግ ካውንቲ ውስጥ የ Prosecuting Attorney (ዐቃቤ ሕግ) በመራጮች ይመረጣል።ተጨማሪ ጠበቆች በታዳጊዎች ክፍል ውስጥ ለመስራት ተቀጥረዋል። ጽ/ቤታቸው የሚገኘው በ **Children and Family Justice Center (CFJC፣ የህፃናት እና የቤተሰብ ፍትህ ማዕከል)** ነው። ፖሊሶች ልጅዎን በቁጥጥር ስር ሲያውሉ፣ ሪፖርቱን ለአቃቤ ህግ ቢሮ ይልካሉ። አቃቤ ህግ ቢሮው የልጁ ጉዳይ በማህበረሰብ ፕሮግራም ማስተናገድ ይቻል እንደሆነ ወይም ጉዳዩ ወደ Court (ፍርድ ቤት) መሄድ እንዳለበት ይወስናል።

**ዐቃቤ ሕግ** - በፍርድ ቤት ውስጥ፣ የዐቃቤ ሕግ ሥራ በልጅዎ ላይ የተፈፀሙት ክሶች ትክክል መሆናቸውን ማረጋገጥ፣ ለማህበረሰብ ደህንነት መሟገት፣ እና በተጠቂዎች ላይ የሚደርሰውን ተጽዕኖ መወከል ነው።እነሱ በሁሉም ችሎቶች ላይ ይሆናሉ/ይገኛሉ። አንዳንድ ጊዜ፣ የተለየ/ሌላ የዐቃቤ ሕግ በእያንዳንዱ ችሎት ላይ ይሳተፋል። የልጅዎ ጉዳይ የቤተሰብ ጥቃትን የሚያካትት ካልሆነ በስተቀር እርስዎ እና ልጅዎ ዐቃቤ ሕጉን ፍርድ ቤት ውስጥ ብቻ ያዩታል።

**የተጎጂ ተሟጋች** - የ Victim Advocates (የተጎጂ ተሟጋቾች) የቤተሰብ አባላትን ጨምሮ በልጁ በተጠረጠረ ወንጀል ለተጎዱ መረጃ፣ ድጋፍ እና ሪፈራል ይሰጣል። (206) 477-3035 ኢሜይል፡- vau.juvenile@kingcounty.gov

**The King County (የኪንግ ካውንቲ) Department of Public Defense (የሕዝብ መከላከያ መምሪያ)**

The Dexter Horton Building (የዴክስተር ሆርቶን ህንፃ)
710 Second Avenue, Suite 200 Seattle, WA 98104
የቢሮ ሰዓታት፦ ከ 8:00am እስከ 5:00pm
ስልክ፦ (206) 296-7662 ወይም ነፃ፦ (844) 935-3534 TTY: 711 Relay Service (711 የማስተላለፍ አገልግሎት)

**Defense Attorney (የመከላከያ ጠበቃ)** ወይም **Public Defender (የሕዝብ ተከላካይ)** - ልጅዎ በወንጀል ከተከሰሰ ወደ ጠበቃ ይመደባል (ይህ ጠበቃ "የሕዝብ ተከራካሪ" ተብሎም ይጠራል)። ይህ ጠበቃ ስራው ልጅዎን በፍርድ ቤት መወከል፣ ለልጅዎ የሕግ ምክር መስጠት እና ልጅዎ ሕጋዊ ውሳኔዎችን እንዲያደርግ ማገዝ ነው። ጠበቃው እርስዎን ሳይሆን ልጅዎን ይወክላል። የጠበቃው ሥራ ልጅዎ ለሚወስነው ነገር መከራከር ነው። ጠበቃው ልጅዎ የሚወስዳቸው ውሳኔዎች ያላቸውን መዘዞች ለልጅዎ ማስረዳት አለበት።የልጅዎ ጠበቃ ልጅዎ ሊያጋራው የማይፈልገውን መረጃ ለእርስዎ እንዲያጋራ አይፈቀድለትም። ይህ ስለተከሰሰው ክስተት፣ ስለ ምስክሮች እና/ወይም ስለልጅዎ የኋላ ታሪክ ያለ መረጃን ሊያካትት ይችላል።

**Mitigation Specialists (የማሻሻል ልዩ ባለሙያዎች)** እና **Paralegals (የሕግ ባለሙያዎች)** ከልጅዎ የመከላከያ ጠበቃ ጋር ይሰራሉ። ስራቸው የአቃቤ ህጉን ስራ ለመደገፍ ማገዝ ነው።

**The King County Superior Court Juvenile Division (የኪንግ ካውንቲ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የታዳጊዎች ክፍል)**
1211 E. Alder St. Seattle, WA
ዋና ፎቅ ሪሴፕሽኒስት (206) 263-8634
ከ 8:15am እስከ 4:30pm ከሰኞ እስከ ዓርብ

Juvenile Court (የታዳጊዎች ፍርድ ቤት) በ King County Superior Court (ኪንግ ካውንቲ ከፍተኛ ፍርድ ቤት) ውስጥ የሚገኝ መምሪያ ነው። ከ Juvenile Detention (ከታዳጊዎች እስር)፣ ከ Department of Public Defense (የህዝብ መከላከያ መምሪያ) እና ከአቃቤ ህግ የተለየ ነው።

## የታዳጊ ፍርድ ቤት ሰራተኞች

ፍርድ ቤቱ ሰዎችን በብዙ የተለያዩ ቦታዎች እንዲሰሩ ይቀጥራል። እነዚህ ግለሰቦች በመምሪያው ውስጥ የተለያዩ ማዕረጎች እና ኃላፊነቶች አሏቸው።

**ዳኞች**- Judges (ዳኞች) በይፋ የተመረጡ ባለሥልጣኖች ናቸው። ሕጋዊ ደምቦች መከተላቸውን ለማረጋገጥ አንድ ዳኛ በእያንዳንዱ የፍርድ ቤት ችሎት ላይ ኃላፊ ነው። ዳኛው ልጅዎ በወንጀል ጥፋተኛ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ይወስናል፣ ልጅዎ በእስር ላይ የሚቆይበትን ጊዜ ይወስናል፣ እና ልጅዎ ቅጣቱን ለመፈፀም ምን እንደሚያደርግ ይወስናል (እንደ የሙከራ ጊዜ፣ **Juvenile Rehabilitation (JR፣ የታዳጊዎች ማገገሚያ)** ወይም የማህበረሰብ አገልግሎት)። እርስዎ እና ልጅዎ በፍርድ ችሎት ወቅት ከዳኛ ጋር ብቻ ነው የሚገናኙት። እንዲሁም በልጅዎ የፍርድ ቤት ችሎት በቀጥታ ከዳኛው ጋር ለመነጋገር እድል ይኖርዎታል። ከዳኛው ጋር ለማጋራት የሚፈልጉት ማንኛውንም መረጃ ለ Intake (ወደ ውስጥ ለሚያስገባው) **Juvenile Probation Counselor (JPC፣ የታዳጊዎች አመክሮ አማካሪ)** መንገር አለብዎት። የ Intake JPCው ስለ ልጅዎ መረጃን ጠቅለል አድርጎ እና ለአያያዝ አማራጮች ለዳኛው ምክረ ሃሳቦችን ይሰጣል።

**የታዳጊዎች የአመክሮ ጊዜ አማካሪዎች** JPC ዎች የልጅዎን ፍላጎት ለማወቅ ይረዳሉ፣ የዳኛውን ትእዛዞች እንዲከተል እና ለዳኛው መልሰው ሪፖርት እንዲያደርጉ ይረዳሉ።

የተለያዩ የ JPC ዓይነቶች አሉ እና በሂደቱ ውስጥ በተለያዩ ጊዜያት ይሳተፋሉ፦

*Screening* Juvenile Probation Counselor (JPC፣ የታዳጊዎች አመክሮ አማካሪ) ማጣራት - ልጅዎ መጀመሪያ ወደ እስር ቤት ሲወሰድ ወላጅ/አሳዳጊውን ቃለ-ምልልስ ያደርጋል።

*Intake Juvenile Probation Counselor (JPC፣ የታዳጊዎች አመክሮ አማካሪ) አስገቢው* ልጅዎን ሊረዱ ይችላሉ ብለው ስለሚያስባቸው የህክምና አገልግሎቶች ለዳኛው ምክሮችን ይሰጣል። ስለ የፍርድ ቤት ሂደት ጥያቄዎች ካሉዎት፣ አስገቢው JPC ሊያነጋግሩት ከሚችሉት የተሻለው ሰው ነው። ዳኛው ስለልጅዎ እንዲያውቅ የሚፈልጉት መረጃ ካለዎት ለአስገቢው JPC ማሳወቅ አለብዎት።

*Supervising Juvenile Probation Counselor (JPC፣ የታዳጊዎች አመክሮ አማካሪ) ተቆጣጣሪ* - ልጅዎ አቅጣጫ በመለወጥ ፕሮግራም ውስጥ ከሆነ ወይም በወንጀል ከተከሰሰ ግን በእስር ላይ ካልሆነ፣ ተቆጣጣሪ JPC ይመደብለታል። ተቆጣጣሪ JPC በልጅዎ ቤት አቅራቢያ በሚገኘው የአመክሮ ጊዜ ቢሮ ውስጥ ይሰራል።

## **ልጅዎ በአመክሮ ጊዜ** ላይ ሲሆን

ፍርድ ቤቱ ልጅዎ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚፈልገውን ድጋፍ ማግኘት ይችላል ብሎ ሲያምን፣ ልጅዎን በአመክሮ ጊዜ ላይ ሊያደርግ ይችላል። አብዛኛዎቹ በወንጀል ጥፋተኛ ብለው የተናገሩ ወይም በወንጀል የተከሰሱ ወጣቶች በማህበረሰቡ ውስጥ ይቆያሉ እና ከታዳጊዎች የአመክሮ ጊዜ አማካሪ ጋር በአመክሮ ጊዜ ጉዳይ ዕቅድ ውስጥ ይሳተፋሉ። ልጅዎ ወደ ትምህርት ቤት እንደመሄድ ያሉ አንዳንድ ህጎችን እንዲከተል ይጠየቃል፣ እንዲሁም ለልጅዎ እና ለቤተሰብዎ በተናጠል ድጋፍ እና አገልግሎቶች ይሰጣቸዋል። ልጅዎ በአመክሮ ጊዜ ላይ ከሆነ፣ የታዳጊዎች የአመክሮ ጊዜ አማካሪ ከእርስዎ እና ከልጅዎ ጋር እንደ የምክር አገልግሎት፣ ቅጥር እና የትምህርት ድጋፍን የመሳሰሉ ነገሮችን ሊያካትት የሚችል አጠቃላይ የጉዳይ ዕቅድ ለማዘጋጀት ይሰራል። የአመክሮ አማካሪዎች ዋና ዓላማ ልጅዎን እና ቤተሰብዎን በሂደቱ መደገፍ ነው። እንዲሁም ወደፊት ጠቃሚ የሚሆኑ ሰላማዊ እና ጤናማ ግብዓቶችንም ያቀርባሉ።

## የአመክሮ ጊዜ መረጃ

የወጣቱን ተቆጣጣሪ የአመክሮ አማካሪ ካወቁ ያንን መኮንን በቀጥታ ማነጋገር ይችላሉ። ካልሆነ ግን ወደ ትክክለኛው ሰው እንዲዘዋወር ለዋናው ሪሴፕሽኒስት ሊደውሉ ይችላሉ።

### የታዳጊዎች አመክሮ ጊዜ ቢሮዎች

**Seattle** (City Unit) (206) 477-4929
1211 E. Alder St. Seattle, WA

**Federal Way** (South II) (206) 477-7360
34004 16th Avenue South #104 Bellevue, WA 98003

**Renton** (South I) (206) 477-5335
451 SW 10th Street #200 Renton, WA 98057

**Bellevue** (Northeast Unit) (206) 477-6490
1722 138th Place NE #200 Bellevue, WA 98005

ስለ JPCዎች ሚና የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ ይህንን ድረ-ገጽ ይጎብኙ።

**The King County Department of Adult and Juvenile Detention (DAJD፣ የኪንግ ካውንቲ የአዋቂዎች እና የታዳጊዎች ማቆያ መምሪያ**

1211 E. Alder St. Seattle, WA

ይህ መምሪያ የታዳጊዎችን እስር ይሰራል። ምንም እንኳን በአንድ ህንፃ ውስጥ ቢሆኑም፣ DAJD ከታዳጊዎች ፍርድ ቤት የተለየ ክፍል ነው። በታዳጊ ወጣቶች ክፍል ውስጥ ከወጣቶች ጋር አብረው የሚሰሩ የ DAJD ሰራተኞች የተመዘገቡ ነርሶች፣ የአእምሮ ጤና ባለሙያዎች፣ የህክምና ረዳቶች፣ መምህራን፣ ታዳጊዎች ማቆያ መኮንኖች፣ የመልሶ ማቋቋም የፍትህ አስተባባሪዎች፣ የአቅጣጫ እና የምዘና ባለሙያዎች፣ የመዝናኛ አስተባባሪዎች፣ የበጎ ፈቃደኞች አስተባባሪዎች እና የእርምት ተቆጣጣሪዎችን ያካትታሉ።

# ልጅዎ ሲታሰር/በቁጥጥር ውስጥ ሲውል

ፖሊሶች ልጅዎን ከያዙ ልጅዎን ወደ ቤት ሊልኩ ይችላሉ፣ እናም ልጅዎ በኋላ ወደ ፍርድ ቤት መምጣት ይኖርበታል።

በሌላ ጊዜዎች፣ ፖሊሶች ልጅዎን ይዘው ወደ እስር ቤት ይወስዷሉ። ፖሊስ በእነዚህ ምክንያቶች ልጅዎን ወደ እስር ቤት ሊወስድ ይችላል፦

1. ፖሊሶች ልጅዎ በጠመንጃ መሳሪያ (ሽጉጥ) ወንጀል እንደፈፀመ ያስባሉ።
2. ፖሊሶች ልጅዎ በትምህርት ቤት ሰራተኛ፣ በአስተዳዳሪ ወይም በአስተማሪ ላይ ጥቃት እንደደረሰ ያስባሉ።
3. ለልጅዎ እስራት **warrant (ዋስትና)** አለ።
4. ፖሊሶች ልጅዎ ሌላ ሰውን ያስፈራራ ነበር ወይም አንድን ሰው ሊጎዳ ወይም ከባድ የንብረት ውድመት ሊያስከትል በሚችል ሁኔታ ውስጥ እንዳለ ያስባሉ።
5. ልጅዎ ከዚህ በፊት ብዙ ጊዜ ተይዟል/ታስሯል፣ እናም ፖሊሶች ስለልጅዎ ወቅታዊ ባህሪ ያሳስባቸዋል።

ፖሊሶች ልጅዎን ወደ እስር ቤት እንዲወስዱ ሊያደርግ የሚችል የተጠረጠሩ ጥፋቶችን ዝርዝር ለማግኘት፣ Juvenile Detention Intake Criteria (የታዳጊዎች ማቆያ መመዝገቢያ/ማስገቢያ መመዘኛዎች) ን ይመልከቱ።

# ልጅዎ ለመጀመሪያ ጊዜ በታዳጊዎች እስር ቤት ሲደርስ ምን ይሆናል

ፖሊሶች ልጅዎን ወደ እስር ቤት ከወሰዱ፣ ልጅዎን በሲያትል ውስጥ በ 1211 E. Alder St ወደሚገኘው የ Children and Family Justice Center (ህፃናት እና የቤተሰብ ፍትህ ማዕከል) ይወስዱታል።

### የህክምና ምርመራ፦

በታዳጊዎች እስር ቤት እንደደረሱ አንድ **ነርስ** ልጅዎን ይመረምራል። ሰራተኞች ስለልጅዎ ጤንነት ወይም የአእምሮ ጤንነት ከባድ ስጋት ካላቸው ልጅዎ ለግምገማ ወደ ሆስፒታል ሊወሰድ ይችላል። ልጅዎ ከባድ የጤና እክል ከሌለው ደህንነቱ ወደ ተጠበቀ እስር ሲደርሱ እንደገና በነርስ ይገመገማል።

አንዴ ልጅዎ ደህንነቱ በተጠበቀ እስር ቤት ውስጥ ከተቀመጠ፣ እንደተመለከተው የሕክምና እንክብካቤ እና የአእምሮ ጤና አገልግሎቶችን ያገኛሉ። የጤና ክሊኒኩ የወጣቶችን ፍላጎት ለመከታተል እና ምላሽ ለመስጠት ሌት ተቀን በስራ ላይ ነው። ልጅዎ ደህንነቱ በጠበቀ እስር ቤት በገባ በ 24 ሰዓታት ውስጥ፣ ልጅዎ ሊወስድ ስለሚችለው ማንኛውም መድሃኒት ማወቅን ጨምሮ ስለጤንነታቸው ታሪክ እና ፍላጎቶች የበለጠ ለማወቅ ነርስ ለወላጆች ይደውላል።

**ከሚያጣራው ሰው ጋር መነጋገር፡-**
ልጅዎ ወደ እስር ቤት ሲወሰድ የፖሊስ መኮንን ወይም የታዳጊዎች አመክሮ አጣሪ አማካሪ JPC) ይደውልልዎታል። "Screener (አጣሪው)" ስጋቶችዎን ያዳምጣል፣ ለጥያቄዎችዎ መልስ ይሰጥዎታል እና ቀጣይ እርምጃዎችን ለመረዳት ይረዳዎታል። **ለልጅዎ ጥብቅና መቆም ጥሩው ሰዓት አሁን ነው።** ስለ ልጅዎ ማወቅ አለባቸው ብለው የሚያስቡትን መረጃ ለአጣሪው ሊያጋሩ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ ልጅዎ የአካል ጉዳት ካለበት ወይም ቤት-አልባ ሆኖ የሚኖር ከሆነ ለአጣሪው ማሳወቅ አለብዎት።

አጣሪው/መርማሪው ይህንን መረጃ ለ Juvenile Detention (**ታዳጊዎች እስር ቤት**)፣ ለ Court (**ፍርድ ቤት**)፣ ለ Prosecuting Attorney's Office (**ለዐቃቤ ሕግ ቢሮ**)፣ እና ለ Department of Public Defense (**የህዝብ መከላከያ መምሪያ**) ያጋራል።

**ልጅዎ በእስር ላይ ይቆያል ወይም ወደ ቤት ይሄዳል፡-**
አጣሪው ከእርስዎ፣ ከልጅዎ እና ከፖሊስ ያወቁትን መረጃ ይወስዳሉ። ከዚያ ልጅዎ በእስር ላይ መቆየት እንዳለበት ወይም ወደ ቤት መሄድ ይችል እንደሆነ ለማየት የፍርድ ቤቱን ህጎች ይመለከታሉ።

አብዛኛውን ጊዜ፣ በሚከተሉት ምክንያቶች ልጅዎ በእስር ላይ መቆየት አለበት፡-

- ፖሊሶች ልጅዎ ከፍተኛ ወንጀል እንደፈፀመ ካሰቡ
- ፍርድ ቤቱ ልጅዎ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚገኝ ከሆነ ስለ ህዝብ ደህንነት ከተጨነቀ
- ፍርድ ቤቱ ልጅዎ ራሱን ሊጎዳ ይችላል የሚል ስጋት ካለው
- ፍርድ ቤቱ ልጅዎ ቀጣይ ስብሰባዎች ላይ አይመጣም ብሎ ከተጨነቀ

**ቀጣይ እርምጃዎች፡-**
አጣሪው/መርማሪው በልጅዎ ሁኔታ ላይ በመመርኮዝ ቀጥሎ ምን እንደሚሆን ይነግርዎታል። ልጅዎ ቀድሞውኑ ከ JPC ጋር ከተሳተፈ፣ JPC በሚቀጥሉት ደረጃዎች ከእርስዎ ጋር አብሮ ይሰራል። ልጅዎ በእስር ላይ ለምን ያህል ጊዜ መቆየት እንዳለበት በልጅዎ ግለሰባዊ ሁኔታ እና በ JPC ዎች፣ በዳኛው፣ እና በአቃቤ ህግ እና በተከላካዮች ጠበቆች በሚሰጡት ውሳኔዎች ላይ የሚመረኮዝ ይሆናል።

## ልጅዎ በቤተሰብ አመፅ/ጥቃት ምክንያት ከታሰረ የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት እና መልሶ ማቋቋሚያ አገልግሎቶች ማዕከል (FIRS)

ልጅዎ በቤተሰብ አባል ላይ በቤት ውስጥ ጥቃት ከተከሰሰ በእስር ላይ ከመቆየት ይልቅ ወደ Family Intervention and Restorative Services Center (የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት እና ማገገሚያ አገልግሎቶች ማዕከል) ለመግባት ብቁ ሊሆን ይችላል። FIRS ማእከል በቤተሰቦቻቸው ላይ ጥቃትን ለሚያደርሱ ወጣቶች በፕሮግራም እና በአገልግሎቶች የተካነ የማህበረሰብ ድርጅት የተከፈተበት ተቋም ነው። ልጅዎ በ FIRS ከተመዘገበ፣ ልጅዎ እና ቤተሰብዎ ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት የባህሪ ጤና አገልግሎቶችን ለመከታተል መደበኛ ባልሆነ ስምምነት ላይ ይሰራሉ። የ FIRS ሰራተኞች ወጣቶችን በደህና ከቤተሰቦቻቸው ጋር ለማገናኘት የሰላም ማስፋፊያ ምክር ይሰጣሉ። ቤተሰቦች ምንም ወጪ ሳያወጡ በቤት ውስጥ የቤተሰብ ምክር፣ የአእምሮ ጤንነት አገልግሎቶች፣ የአደንዛዥ ዕፅ እና የአልኮል አገልግሎቶች እና የ Step-Up Program (የእድገት ደረጃ ፕሮግራም) ን በተለይ በጉርምስና ዕድሜያቸው በቤተሰብ ላይ የሚደርሱትን ጥቃት የሚዳስስ አገልግሎቶች ይሰጣቸዋል። FIRS ማዕከል ደህንነቱ የተጠበቀ እስር አይደለም ነው።

ልጅዎ ለ FIRS ብቁ ከሆነ፣ አጣሪው/መርማሪው ይህንን አማራጭ ከእርስዎ ጋር ይወያያል። ልጅዎ ወደ FIRS የሚገባው እርስዎ እንደ ወላጅ/አሳዳጊ ከተስማሙ ብቻ ነው። ስለ FIRS በድረ-ገጻቸው ላይየበለጠ ይወቁ።

FIRS ማዕከል (ወጣቶች የሚቆዩበት ተቋም) (206) 474-7373 FIRS ፕሮግራም ተቆጣጣሪ (206) 477-6528

# ልጅዎ በእስር ላይ ከሆነ ምን ማድረግ ይችላሉ

**ወዲያውኑ ልጅዎን ለመጎብኘት ይሞክሩ።** በአንድ ጊዜ ለግማሽ ሰዓት ያህል በሳምንት እስከ ሦስት ጊዜ ሊጎበኙ ይችላሉ። በመጀመሪያ ጉብኝት ልጅዎ የታዘዘለትን መድሃኒት ይዘው ይምጡ። ምግብ፣ ልብስ፣ ገንዘብ፣ ወይም የግል ዕቃዎች ወደ መጎብኛው ቦታ ሊመጡ አይችሉም። አንድ ወላጅ ወይም አሳዳጊ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲጎበኙ በማንኛውም ሰዓት መምጣት ይችላሉ።ከዚያ ጉብኝት በኋላ መደበኛ የጉብኝት ሰዓቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

3:30pm እና 9:00pm በስራ ቀናት
9:00am እና 2:30pm እና ከ 3:30pm እስከ 9pm በእረፍት ቀናት እና በበዓል ቀናት

**ልጅዎ በ defense attorney (የመከላከያ ጠበቃ) የመወከል መብቱን ይገንዘቡ።** የልጅዎ ተከላካይ ጠበቃ የልጅዎን ፍላጎቶች እና ውሳኔዎች ይወክላል። ልጅዎ ከእስር እንዲለቀቅ እና አነስተኛ ክሶችን እንዲቀበሉ ይከራከራሉ። **ልጅዎ ለተከላካይ ጠበቃቸው ሐቀኛ እንዲሆን ይንገሩ።**

**ፖሊስ ልጅዎን ከመያዙ በፊት እና በኋላ ጥያቄ ይጠይቃል።** በኪንግ ካውንቲ ውስጥ፣ ፖሊስ የልጁ ተከላካይ ጠበቃ ሳይኖር በታዳጊዎች እስር ቤት ልጁን ቃለ መጠይቅ ማድረግ/መጠየቅ አይችልም። በታዳጊዎች እስር ቤት በሚደረገው ቃለ መጠይቁ ወቅት ልጅዎ ዝም የማለት እና እርስዎን እና ጠበቃውን በመጠይቁ ላይ የማስገኘት መብት አለው።

**የስልክ ጥሪዎችን በተቻለ ፍጥነት ይመልሱ።** የሚሰራ የስልክ ቁጥር ከሌለዎት፣ ለፍርድ ቤቱ እና ለተከላካዩ ጠበቃ የታመነ ጓደኛዎን ወይም የቤተሰብ አባል ስልክ ቁጥርን ይስጡ። ሁሉንም ጥሪዎች በተቻለዎት ፍጥነት ይመልሱ እና በስምዎ እና በተመላሽ ስልክ ቁጥርዎ መልዕክቶችን ይተዉ። እንዲሁም ኢሜይል መጠቀም ይችላሉ።

# ለልጅዎ ጥብቅና መቆም

ልጅዎ ህጉን ጥሷል ተብሎ በሚጠረጠርበት ጊዜ ለልጅዎ መገኘት እና ድጋፍ መስጠት አስፈላጊ ነው። ልጅዎ እርስዎን ወይም ሌላ የቤተሰብ አባልን ጎድቶ ሊሆን ይችላል እናም የልጅዎ ባህሪ ከእርስዎ ቁጥጥር በላይ የሆነ ሊመስል ይችላል። ይህ ልጅዎ ግንኙነትዎን እንደገና ለመገንባት እና ለቤተሰብዎን ሕይወት ለማሻሻል የሚያስፈልገውን እርዳታ እንዲያገኝ እድል ሊሆን ይችላል። ለመማር ብዙ ዕድሎችን ይፈልጉ ይሆናል፣ እናም በዚህ ሂደት ውስጥ፣ በሕይወታቸው ውስጥ አሳቢ እና ደጋፊ የሆኑ የጎልማሳ ግንኙነቶች ይፈልጋሉ። እርስዎ መገኘት ካልቻሉ፣ ስርዓቱ እርስዎን እንዲወክሉ ከፈቀዱት ሌሎች አዋቂዎች ጋርም ይሰራል።

**ልጅዎ የአካል ጉዳት ካለበት፡-** ልጅዎ በእስር፣ በፍርድ ቤት እና በትምህርት ቤት ውስጥ የማረፊያ ቤት ሕጋዊ መብቶች አሉት። ልጅዎ ለይቶ የታወቀ የአካል ጉዳት ካለበት፣ ከታዳጊዎች ማቆያ ማዕከል፣ ከት/ቤቱ እና ከፍርድ ቤቱ ማረፊያዎችን መጠየቅ ይችላሉ። CFJC የ Americans with Disabilities Act (ADA፣ የአሜሪካ የአካል ጉዳተኞች ሕግ) መስፈርቶችን ያሟላል።

**ልጅዎ ግብረሰዶማዊ፣ ባይሴክሹዋል፣ ትራንስጀንደር ወይም ኲዊር ከሆነ፡-** በኪንግ ካውንቲ የተለያዩ ክፍሎች ውስጥ ያሉ ባለሞያዎች የ LGBTQ (ኤል. ጂ. ቢ. ቲ. ኪው) ወጣቶችን የሚያካትት ልዩ ስልጠና ይሰጣቸዋል። ስለልጅዎ ማንነት የበለጠ ባወቁ ቁጥር ፍላጎታቸውን ማሟላት ይችላሉ። በታዳጊዎች እስር ውስጥ፣ ወጣቶች በጾታ ማንነታቸው ይለያሉ። [እዚህ የበለጠ ያንብቡ]።

**የሚፈልጉትን ይጠይቁ፡-** ወላጆች በሕጋዊ ሥርዓት ውስጥ የተሳተፈ ልጅ ሲኖራቸው፣ ከስራ፣ ከምክር አገልግሎት፣ ከምክር ፣ ከሀብት እና ከልጆች አጠባበቅ ጊዜን በመውሰድ ብዙ ድጋፍ ይፈልጋሉ። እርስዎ እንዲሳተፉ ፍርድ ቤቱ ይፈልጋል እናም መቻልዎን ለማረጋገጥ የሚቻለውን ሁሉ ያደርጋል። ይህ ቤተሰብዎ ወይም ልጆችዎ ከሚፈልጓቸው አገልግሎቶች ጋር ለመገናኘት እድል ሊሆን ይችላል። ፍላጎቶችዎን ለማሟላት (ለምሳሌ እንደ ቤት፣ ምግብ፣ ልብስ) ወይም ወደ ስብሰባዎች ለመድረስ በሚቸገሩበት ጊዜ ለሚመለከታቸው ባለሙያዎች መንገርዎን ያረጋግጡ። እነሱ ወደ ሚያውቋት ሀብቶች በመምራት

እና በአማራጮችዎ ላይ በመወያየት ይረዱዎታል። ባለሙያዎች ፍላጎቶችዎን በተሻለ በተረዱበት መጠን፣ የበለጠ ሊረዱዎት ይችላሉ።

**ተዘጋጅተው ይቆዩ፡-** የሕግ ሂደቱ በጣም ግራ የሚያጋባ ሊሆን ይችላል።ብዙ ሰዎች እርስዎን ለመርዳት ይፈልጉዎታል እናም እነሱ የተለያዩ ሚናዎች ይኖራቸዋል። የሚመለከታቸው ሰዎችም እንደ ሁኔታው ይለወጣሉ። ከልጅዎ ጋር አብረው የሚሰሩ ሰዎችን ስም፣ የስራ ድርሻ፣ የቢሮ ስም እና የስልክ ቁጥር መፃፍዎን ያረጋግጡ። እነዚህን ሁሉ መረጃዎች በአንድ ላይ የሚይዙበት አንድ ማስታወሻ ደብተር ቢኖርዎት ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።ሁሉንም ሰነዶችዎን በሚያስቀምጡበት በዚህ ማስታወሻ ደብተር አንድ አቃፊ/ማቀፊያ ይያዙ።መረጃን በጽሑፍ እና ለመረዳት ቀላል በሆኑ መንገዶች ይጠይቁ።

**ጥያቄዎችን ይጠይቁ፡-** የሕግ ሥርዓቱ ውስብስብ ነው! ከረሱ ወይም ካልተረዱ ብዙ ጥያቄዎችን ማቅረብ እና ተመሳሳይ ጥያቄን ብዙ ጊዜ መጠየቅ ምንም ችግር የለውም። ባለሙያው ለጥያቄዎ መልስ ካላወቀ ወደ ሚያውቅ ሰው ይመራዎታል።

**ስብሰባዎችን እና ፍርድ ቤት ችሎቶችን መሳተፍ እና በሰዓት መድረስ፡-** በሰዓቱ መድረስ ካልቻሉ ወይም እንደዘገዩ ከገባዎት ስብሰባ ላልዎት ሰው ወይም ሰዎች ቢሮ ይደውሉ። እርስዎ መገኘት በሚችሉበት ጊዜ እንዲደውልሉዎት የስራ ሁኔታዎን እና ሰዓታትዎን ለባለሙያዎች ይንገሩ።

**ስለ ልጅዎ በሁሉም ውሳኔዎች ውስጥ ይሳተፉ፡-** በሚቻልበት ጊዜ ሁሉ ይሳተፉ። የማይመች ወይም የሚያስፈራ ቢመስልም፣ በልጅዎ ፍላጎቶች ላይ ግብዓት ለመስጠት በስብሰባዎች ላይ ይናገሩ። ሰዎች መረጃን ያውቃሉ ወይም ይጋራሉ ብለው አያስቡ። አንዳንድ ጊዜ፣ ባለሙያዎች መረጃዎችን እርስ በርሳቸው እንዳይጋሩ በሕግ የተከለከለ ነው።

**በፍርድ ቤት ይሳተፉ፡-** ለራስዎ በመሟገት ወይም አስፈላጊ ነው ብለው የሚያስቡትን መረጃዎች በመጨመር ለመሳተፍ ዝግጁ ይሁኑ። የእርስዎ አስተያየት ከጠበቆች ወይም ከአመክሮ አማካሪዎች 'የተለየ ሊሆን ይችላል። የእርስዎን አስተያየት ግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው። ድጋፍ ለማግኘት አንድ የታመነ አዋቂ ወይም የቤተሰብ አባላት ይዘው መምጣት ይችላሉ።

**የልጅዎ ጉዳይ ከሚመለከታቸው ሰዎች ጋር አክብሮታዊ ግንኙነቶችን ይገንቡ፡-** ስለ ልጅዎ ሁኔታ ወይም ስለ ግለሰቡ ባለሙያ ምንም ዓይነት ስሜት ሊሰማዎት ቢችልም ሁልጊዜ በአክብሮት መግባባት አለብዎት። አክብሮት የጎደለው ሆኖ ከተሰማዎት ወይም አግባብ ባልሆነ መንገድ እንደተስተናገዱ የሚያምኑ ከሆነ፣ ጉዳዩ የሚመለከተውን አካል ተቆጣጣሪ ያነጋግሩ። ሂደቱ አንዳንድ ጊዜ በጣም አስጨናቂ ይሆናል፣ እናም ግንኙነቶችን የመፍጠር ችሎታዎ እርስዎን እና ልጅዎን ይረዳል። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ድጋፍ መፈለግ እና ጥያቄዎችን መጠየቅ አስፈላጊ ነው።

# በታዳጊዎች እስር ቤት ምን ይከሰታል?

**1211 E. Alder St Seattle, WA**

እስር በአዋቂዎች እና የታዳጊዎች ማቆያ መምሪያ (DAJD) የሚሰራ የተቆለፈ ህንፃ ነው። ልጅዎ የፍርድ ቤቱን ችሎት በሚጠብቅበት ወይም ቅጣቱን በሚጠብቅበት ጊዜ በእስር ላይ ሊሆን ይችላል። ወደ እስር ቤት መሄድ አስፈሪ ተሞክሮ ሊሆን ይችላል እና በተለይም ምን መጠበቅ እንዳለብዎት ካላወቁ በጣም አስፈሪ ሊሆን ይችላል። የታዳጊዎች ማቆያ ማዕከላት ስለ ደህንነት፣ በታ፣ ጤና እና መዝናኛ ጥብቅ ደንቦችን መከተል አለባቸው።

ልጅዎ ደህንነቱ ወደ ተጠበቀ እስር ቤት እንዲጠበቅ ከተላከ፣ የእስር ቤቱ ሰራተኞች ልብሶቻቸውን እና የግል ንብረቶቻቸውን በማከማቻ ክፍል ውስጥ ያስቀምጣሉ። ሰራተኞች የተከለከሉ ዕቃዎችን እንደማያመጣ ለማረጋገጥ ልጅዎን ይፈትሹታል። ልጅዎ ገላዎን ይታጠባል እና ሰራተኞች ንጹህ የልብስ ይሰጡታል። አልባሳት ቲሸርት፣ ቶፕ፣ ሱሪ፣ የውስጥ ሱሪ፣ ካልሲ እና ጥንድ ስሊፐሮችን ያካትታሉ።ሰራተኞች ለልጅዎ ንፁህ አንሶላ እና ብርድ ልብስም ጭምር ይሰጡታል። ልጅዎ ከሚለይበት መረጃ ጋር የደህንነት አምባር ይሰጠዋል።የጤና እንክብካቤ ሰራተኞች ልጅዎን ቃለ-መጠይቅ ይጠይቃሉ እና የአካል እና የአእምሮ ጤንነት ምርመራ ያካሂዳሉ። የማቆያ ሠራተኞች ልጅዎን በእስር ላይ እያሉ የአደንዛዥ ዕፅ ምርመራ አያደርጉለትም፣ ነገር ግን ከከፍተኛ ፍርድ ቤት የታዳጊዎች አመክሮ ጊዜ ሊወስድ ይችላል።

በመቀጠል ልጅዎን ቃለ-መጠይቅ ከሚያደርግለት፣ መብቶቻቸውን፣ ደንቦቻችን፣ ምን እንደሚጠብቁ እና በጾታ ማንነት፣ ዕድሜ፣ መጠን እና እንደተከሰሰበት ወንጀል እና የልጅዎ የቀድሞ ባህሪ ያለ ሌላ ታሪክ ላይ በመመርኮዝ ለመኖር በጣም ደህንነቱ የተጠበቀ የመኖሪያ አዳራሽ ከሚወስን የ Orientation and Assessment Specialist (የአቅጣጫ እና ምዘና ባለሙያ) ጋር ይገናኛል።

የልጅዎ ደህንነት (አካላዊ፣ ስሜታዊ፣ እና ወሲባዊ) የታዳጊዎች እስር ቤት ሰራተኞች ቁጥር አንድ ቅድሚያ የሚሰጡት ጉዳይ ነው። በእስር ላይ ያለ ሌላ ልጅ የልጅዎን ደህና መሆን ወይም ደህንነት ላይ አደጋ የሚጥል ከሆነ ለአካለ መጠን ያልደረሱ የማቆያ ሠራተኞች መፍትሄ ይሰጡታል። የታዳጊዎች ማቆያ ሰራተኞች ምንም አይነት መሳሪያ አልታጠቁም እና አካላዊ ቅጣትን፣ ትንኮሳዎችን፣ ዘቻዎችን፣ ጉዳቶችን ወይም ማንቋሸሽን አይጠቀሙም። ጠብ ካለ፣ ሰራተኞቹ እገዳዎችን ወይም ሀይልን ከመጠቀም በፊት የማስወገጃ ዘዴዎችን እንዲጠቀሙ ሰልጥነዋል። የሁሉንም ሰው ደህንነት ለመጠበቅ፣ የታዳጊዎች እስር ቤት የሚከተሉትን ባህሪ ይጠብቃል፦

- ሁሉንም የትምህርት ቤት ክፍለ-ጊዜዎች መሳተፍ
- በሌሎች መርሃግብሮች ውስጥ በአዎንታዊ መልኩ መሳተፍ
- አክብሮት ማሳየት
- ከሌሎች ጋር መግባባት/መስማማት
- እጆችዎን እራስዎ ጋር ማቆየት
- ደጋፊ ቋንቋን መጠቀም
- ሰራተኞች የሚጠይቁትን ማድረግ
- በአዎንታዊ እና በፍጥነት መልስ መስጠት
- አክባሪ ቋንቋን መጠቀም
- በየቀኑ ገላን በመታጠብ ንፅህናን መጠበቅ
- አልጋውን በማንጠፍ፣ ቆሻሻውን በማውጣት፣ እና እቃዎችን በማስተካከል ክፍሉን በንፅህና መጠበቅ

ወጣቶች ከባህሪይ የሚጠበቁ ነገሮችን ሲያሟሉ፣ በየቀኑ ልዩ መክሰሶች፣ የ MP3 ማጫወቻ ኪራዮች፣ እና አዲስ የስፖርት ማዘውተሪያ ጫማዎችን ለመግዛት የሚያገለግሉ "ኮከቦችን" ማግኘት ይችላሉ። በተጨማሪም፣ ወጣቶች በየቀኑ አነስተኛ ቁጥር ያላቸውን ኮከቦችን ካገኙ በኋላ፣ የክብር ደረጃ እንቅስቃሴዎችን፣ የቪዲዮ ጌም/ጨዋታ ጊዜን ወይም ቅናሽ የተደረገበት የመክሰስ ዝርዝር ያገኛሉ።

የወጣትነት ባህሪ ደህንነትን አደጋ ላይ የሚጥል ከሆነ፣ ከእኩዮች ጋር ችግርን የመፍታት ወይም የይቅርታ ደብዳቤ መጻፍ ባሉ የመልሶ ማቋቋም ተግባራት ውስጥ እንዲሳተፉ እድል ይሰጣቸዋል። ወጣቶች እንደ የተራዘመ የመኝታ ጊዜ ወይም "honor level status (የክብር ደረጃ ሁኔታ)" ያሉ መብቶችን ሊያጡ ይችላሉ። ወጣቶች እንደ ትንኮሳ፣ ንብረት ማውደም፣ ወይም አካላዊ ወይም ወሲባዊ ጥቃቶች በመሳሰሉ ባህሪዎች ውስጥ ከተሳተፉ በ Restoration Hall (የመልሶ ማቋቋም አዳራሽ) ውስጥ የፕሮግራም ጊዜ ሊያሳልፉ ይችላሉ። በመልሶ ማቋቋም አዳራሽ ውስጥ ወጣቶች በትምህርት ቤት ውስጥ ይሳተፋሉ እና እንደ መረጋጋት፣ ቁጣን የመቆጣጠር፣ ወይም ስሜትን የመቆጣጠር የመሳሰሉ አዳዲስ ችሎታዎችን ለመማር በልዩ ፕሮግራም ውስጥ ይሳተፋሉ።

ወጣቶች መብቶቻቸው እንደተጣሱ ከተሰማቸው ወዲያውኑ **grievance (ቅሬታ)** እንዲያቀርቡ ይበረታታሉ። የእስር ተቆጣጣሪዎች ሁሉንም ቅሬታዎች ይገመግማሉ፣ ይመረምራሉ እንዲሁም በ 24 ሰዓታት ውስጥ ምላሽ ይሰጣሉ። ቅሬታዎች ምስጢራዊ ናቸው። ቅሬታ የሚቀርብባቸው በቤተ-መጽሐፍት፣ በጂም እና በጤና ክሊኒክ ውስጥ የቅሬታ ቅጾች ያላቸው ሦስት ሳጥኖች አሉ። ሰራተኞች በየምሽቱ አዳዲስ ቅሬታዎች እንዳሉ ይፈትሻሉ።

ደህንነቱ በተጠበቀ እስር ውስጥ ህመሞችን ወይም ጉዳቶችን ለመመርመር እና ለማከም ዝግጁ የሆነ የሙሉ ሰዓት ነርስ ጋር አንድ **የጤና ክሊኒክ** አለ። ልጅዎ ከተጎዳ ወይም ከታመመ፣ ነርሷ/ሱ ልጅዎን ወደ የሕክምና አገልግሎት አቅራቢ ሊልክ ይችላል ወይም ወደ ሆስፒታል መሄድ እንዳለባቸው ሊወስን ይችላል። በዋሺንግተን ግዛት ውስጥ፣ ያለ አሳዳጊ ፈቃድ ወጣቶች ለ [ተወሰኑ የህክምና አገልግሎቶች] ፈቃድ መስጠት ይችላሉ። ልጅዎ ማንኛውንም መድሃኒት የሚወስድ ከሆነ በእስር ላይ እያለ መድሃኒቱን ከነርስ ይቀበላል። ከልጅዎ ጋር ለመገናኘት፣ ልጅዎ ከጠየቀ ወይም ሰራተኞቹ አስሳቢ ባህሪን (ለምሳሌ በራስ ላይ

ጉዳት የማድረስ) ካስተዋሉ የአእምሮ ጤና ሰራተኞች አሉ። የአእምሮ ጤንነት ሰራተኞች ልጅዎ ደህንነቱ በተጠበቀ እስር ውስጥ እንዲሆን የሚደረገውን ሽግግር ሊደግፉ እና ለቀጣይ የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች የሚያስፈልጉትን ነገሮች ለይተው ማወቅ ይችላሉ።  ልጅዎ ወደ እስር ቤት ከመድረሱ በፊት የአእምሮ ጤንነት አገልግሎቶችን እየተቀበለ ከነበረ እባክዎን ስለዚህ ጉዳይ ለህክምና ወይም ለአእምሮ ጤና አገልግሎት ሰጭዎች ያሳውቁ።  የአእምሮ ጤና አገልግሎት በዋሽንግተን ዩኒቨርሲቲ Department of Psychiatry and Behavioral Sciences (የአእምሮ ሕክምና እና የስነምግባር ሳይንስ ክፍል)ይሰጣል።

**የእስር ቤት የጊዜ ሰሌዳ ምሳሌ፡-**

| | |
|---|---|
| ቁርስ/የትምህርት ቤት ዝግጅት | 8:00am – 8:30am |
| ትምህርት ቤት | 8:30am – 11:20am |
| ምሳ እና ማፅዳት | 11:50 am – 12:35 pm |
| ትምህርት ቤት | 12:45pm – 2:45pm |
| የሰራተኛ መቀየር | 2:30pm - 3:30pm |
| ፕሮግራም/ጂም | 3:30pm – 5:00 pm |
| እራት እና ማፅዳት | 5:00 pm – 5:45 pm |
| ፕሮግራም/ጂም | 5:45 pm – 8:00 pm |
| የመኝታ ሰዓት | 8:00pm - 10:00pm |

ደህንነቱ በተጠበቀ እስር ላይ ያሉ ወጣቶች በሳምንቱ ቀናት ሁሉ በ Seattle Public School's Interagency Academy (የሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤት የኢንትራኤጀንሲ አካዳሚ) የሚሰጥ ትምህርት ይማራሉ። ለዕድሜያቸው፣ በማህበረሰቡ ውስጥ በትምህርት ቤት መሻሻል፣ እና ቀደም ሲል ለነበረው የስኬት ደረጃ እንደሚመጥን በንባብ፣ በቋንቋ ጥበባት፣ በሂሳብ፣ በሳይንስ እና በሕይወት ክህሎቶች ትምህርቶችን ይቀበላሉ።አስፈላጊ ከሆነ የልዩ ትምህርት ትምህርቶች ይገኛሉ። ወጣቶች በማቆያ ትምህርት ቤት ውስጥ ወደ General Equivalency Diploma (G.E.D.፣ አጠቃላይ የእኩልነት ዲፕሎማ) አቅጣጫ ሊሰሩ ይችላሉ። ክፍለ-ጊዜዎች ግዴታ ናቸው።

የ King County Library System (የኪንግ ካውንቲ የቤተ መፃህፍት ሥርዓት) ደህንነቱ በተጠበቀ እስር ውስጥ **የቤተ-መጽሐፍት** ቅርንጫፍ ይሰራል። ሁሉም ወጣቶች በተመደቡ ቀናት ቤተ-መጻሕፍትን ለምርምር ፕሮጄክቶች ወይም መጻሕፍትን ለመዝናኛ ለማንበብ ይችላሉ።

እንዲሁም ከቄስ ጋር ለመነጋገር ከፈለጉ ለወጣቶች የምክር አገልግሎት እና መንፈሳዊ መመሪያን የሚያቀርብ Chaplaincy Program (የሃይማኖት አለቆች) አለ። ወጣቶች መሳተፍ ከፈለጉ የክርስቲያን እና የሙስሊም ሃይማኖታዊ አገልግሎቶች ይሰጣሉ።

በእስር ውስጥ ተጨማሪ ፕሮግራሞችን የሚሰጡ ብዙ የአገር ውስጥ ድርጅቶች አሉ። የዚህ መርሃግብር ምሳሌዎች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፡- ዮጋ፣ ግጥም፣ ጥበባት እና የእጅ ሥራ ፕሮጄክቶች፣ የፈጠራ ጽሑፍ፣ የመካሪ፣ የፈጠራ ሥራዎች ፣ የፊልም ምሽቶች፣ የፊልም ሥራ ፕሮጄክቶች፣ የድምፅ ታሪክ ንግረት፣ የAA ስብሰባዎች፣ የእይታ ጥበብ ክፍሎች፣ የቅርጫት ኳስ ክሊኒኮች እና ካምፖች፣ በአሰቃቂ ሁኔታ የተነገሩ የጂምናዚየም ትምህርቶች፣ የአትክልት ስፍራዎች፣ የሰላም ማስከበር ክበብ እና ሌሎችን ያካትታሉ።

**የእስር ማጣሪያ/ምርመራ** (206) 263-9595 (በቀን 24 ሰዓታት/በሳምንት 7 ቀናት)
ልጅዎ ከታሰረ ለእስር ምርመራ/ማጣሪያ እና የልጁን የማቆያ ሁኔታ እና የሚቀጥለውን የችሎት ቀን እና ሰዓት ማወቅ ካስፈለግዎት ይደውሉ።

**የእስር ቤት መረጃ** (206) 477-9890 (በቀን 24 ሰዓታት/በሳምንት 7 ቀናት)
ከእስር ቤት ጋር ለተዛመደ ሌላ መረጃ።

**የጤና ክሊኒክ** (206) 477-9928

## ልጁ በደል ወይም ቸልተኝነትን ሪፖርት ካደረገስ?

እንደ አስተማሪዎች ፣ አማካሪዎች ፣ ማህበራዊ ሰራተኞች ፣ የጉዳይ አስተዳዳሪዎች፣ ተሟጋቾች ፣ ወዘተ ያሉ ከልጆች ጋር የሚሰሩ አብዛኛዎቹ ጎልማሶች (defenders (**ተከላካዮችን**) ሳይጨምር) mandated reporters (**የግዴታ ሪፖርተሮች**)ናቸው። ይህ ማለት ልጅዎ ወይም ሌላ ልጅ እንደተጥቅቃ ከተናገረ፣ ይህ አዋቂ ለ Child Protective Services (CPS፣ **ለልጆች ጥበቃ አገልግሎት**) በዋሽንግተን ግዛት ለሚሰራ Department of Children Youth and Families (DCYF፣ **የህጻናት ወጣቶች እና ቤተሰቦች መምሪያ**) መንገር አለበት። ወጣቶች ይህንን መረጃ በሕግ ሥርዓት ውስጥ ካሉ ባለሙያዎች ጋር ማጋራት የተለመደ ነው።

ከልጁ ወይም ከአዋቂው ፈቃድ ባይሰጣቸውም የግዴታ ሪፖርተሩ ለ CPS መንገር አለበት። ሪፖርት ካላደረጉ ሊባረሩ ወይም ሊታሰሩ ይችላሉ። የግዴታ ሪፖርተሩ የራሳቸውን ፍርድ መጠቀም የለበትም። አንድ ልጅ እየተጠቃሁ ነው ካለ የግዴታ ዘጋቢው ለ CPS መንገር አለበት። CPS ቀጥሎ ምን ማድረግ እንዳለበት ይወስናል።

CPS የጥቃት ሪፖርት ሲያገኝ፣ ለወደፊቱ የ CPS ሰራተኞች የሚገኝ ሪፖርትን በመጻፍ ይጀምራሉ። ያለፉትን የጥቃት ሪፖርቶች ካሉ ያያሉ። ከዚያ፣ እነሱ መመርመር ካለባቸው ይወስናሉ። ምርመራ ካካሄዱ፣ ልጁን እና መረጃ ሊኖራቸው ለሚችል ሌሎች ሰዎች ቃለ መጠይቅ ያጠይቃሉ።እነሱ ልጁ ወይም ሌሎች በቤተሰቡ ውስጥ ያሉ ሰዎች የበለጠ ድጋፍ ይፈልጋሉ ብለው ይወስናሉ። ከፖሊስ ጋር ይነጋገሩ ይሆናል። እንዲሁም ቤተሰቡ እና ልጁ ድጋፍ እንደማይፈልጉ መወሰን ይችላሉ።

CPS ቤተሰቡ ድጋፍ እንደሚያስፈልገው ከወሰነ፣ የልጆች ወጣቶች እና ቤተሰቦች መምሪያ ሰራተኞች ድጋፍ ይሰጣሉ። አብዛኛውን ጊዜ፣ ከወላጆቻቸው/ከአሳዳጊዎቻቸው ጋር ስብሰባዎች ያደርጋሉ፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች የልጁን ደህንነት ለመጠበቅ ምን ማድረግ እንዳለባቸው እቅድ ያወጡ እና ይህን ማድረጋቸውን ለማረጋገጥ ወላጆቻቸውን/ አሳዳጊዎቻቸውን ይከታተላሉ። DCYF እንደቤተሰብ ሕክምና ወይም በማህበረሰቡ ውስጥ ላሉ ሌሎች አገልግሎቶች ግንኙነቶችን ለመፍጠር ለምሳሌ ቤት፣ ምግብ፣ ወይም ሥራ ለማግኘት እርዳታን ሊያቀርብ ይችላል።

አንዳንድ ጊዜ፣ DCYF ቤተሰቦችን ይለያል። በሚቻልበት ጊዜ፣ ልጁ ከቅርብ የቤተሰብ አባል ጋር የሚቆይበትን አስተማማኝ ቦታ ለማግኘት ከወላጆች ጋር አብረው ይሰራሉ።ብዙውን ጊዜ፣ ቤተሰቦች የሚለያዩት ለጥቂት ቀናት ብቻ ነው። ይህ የሚከናወነው ትንንሽ ልጆችን ለመጠበቅ፣ እና በቤተሰብ አባላት ፈጣን እርምጃ እንዲወሰድ ለማድረግ ነው።DCYF ልጁ ከ 3 የስራ ቀናት በላይ ከቤተሰቡ መነጠል አለበት ብሎ ካሰበ፣ የፍርድ ቤት ችሎት ሊኖራቸው ይገባል። ጥቂት ጊዜ፣ ልጆች ረዘም ላለ ጊዜ ከቤተሰቦቻቸው ተለይተዋል። ይህ የቤተሰብ አባላት ለልጆቻቸው ደህንነቱ የተጠበቀ አከባቢን መስጠት በማይችሉበት ጊዜ፣ በጣም ከባድ በሆነ ጥቃት እና ቸል የመባል ጉዳዮች ውስጥ ይከሰታል። በተለምዶ፣ ልጆች ቤተሰቡን ለመደገፍ ብዙ ሙከራዎች ከተደረጉ በኋላ ብቻ ከቤተሰብ የሚለዩት ለረጅም ጊዜ ነው።

የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎን https://www.atg.wa.gov/child-abuse-neglect ን ይጎብኙ።

**ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን ጥቃት ወይም ቸል መባልት ሪፖርት ለማድረግ** (866) END-HARM።

# የፍርድ ቤቱ ሂደት

# የታዳጊ ፍ/ቤቶችን ለመጎብኘት ጠቃሚ ምክሮች

ፍ/ቤቱ ከጠዋቱ 8:30am እስከ 4:30pm ድረስ ለችሎት ክፍት ነው

ድጋፍ ለማግኘት ጓደኞችን ወይም የቤተሰብ አባላት ይዘው መምጣት ይችላሉ። የፍርድ ቤት ጉዳዮችን በሚጠብቁበት ጊዜ ለህፃናት እንክብካቤ ተብሎ የሚሰጥ ቦታ አለ።ፍላጎቶችዎን ለማሟላት አገልግሎቱ መገኘቱን ለማረጋገጥ እባክዎ ከፍርድ ቤቱ ያረጋግጡ።

**አቅጣጫዎች፡-** [ለጎግል ካርታዎች እዚህ ጠቅ ያድርጉ]() ወይም [ለ King County Metro የመስመር ላይ ጉዞ ዕቅድ አውጪ]()ን ጠቅ ያድርጉ

**የመኪና ማቆሚያ፡-** ለጎብኚዎች በቦታው ላይ ነፃ የመኪና ማቆሚያ አለ። በመንገድ ላይ ካቆሙ፣ በ 2 ሰዓት የመኪና ማቆሚያ ዞን ውስጥ ማቆምዎን ያረጋግጡ።

ወደ ተቋሙ **ሲደርሱ**፣ በብረት መርማሪ በኩል ያልፋሉ። በልጅዎ ጉዳይ ላይ የሚሰሩ ሰራተኞች እርስዎ በህንፃው ውስጥ እንዳሉ እንዲያውቁ ሲደርሱ በፍርድ ቤት አገልግሎቶች ሰራተኛ የመረጃ ጠረጴዛው ላይ ፈርመው መግባት አለብዎት። ከችሎቱ በፊት ልጅዎ ከተከላካዩ ጠበቃ ጋር እና ከተሳተፈ ደግሞ ከ JPC እና ከተጠቂው **ተሟጋች** ጋር ለመገናኘት እድል ያገኛል።

**ለመጠበቅ ይዘጋጁ፡-** ወደ ፍርድ ቤት ከመጠራትዎ በፊት ብዙ ሰዓታት ሊጠብቁ ይችላሉ። በሁለተኛው ፎቅ ላይ ቡና፣ መክሰስ እና የተዘጋጁ ምግቦችን የሚያቀርቡበት ካፌ አለ።በአንደኛው ፎቅ ላይ መክሰስ እና መጠጥ ያላቸው የሽያጭ ማሽኖችም አሉ። በአቅራቢያ ያሉ ብዙ ምግብ ቤቶችም አሉ።

**አለባበስ፡-** ዘንጠው መልበስ አያስፈልግዎትም! የልብስ ሀብቶች ከፈለጉ፣ እባክዎን በ (206) 263-8634 ይደውሉልን።

**መሳሪያዎች፡-** ሽጉጦች፣ ቢላዎችን፣ መሣሪያዎችን እና ሌሎች መሣሪያ መሰል መሳሪያዎች በፍርድ ቤት ውስጥ አይፈቀዱም። ወደ ፍ/ቤቱ የሚገባ ማንኛውም ሰው በብረት መርማሪ በኩል ማለፍ ይጠበቅበታል።የደህንነት ስጋቶችን የሚያነሳ ነገር በደህንነት ሰራተኞች ከተገኘ፣ እቃውን ይይዙልዎታል እናም ከህንፃው ሲወጡ እንደገና መውሰድ ይችላሉ።


# የፍርድ ቤት ችሎቶች

### የታዳጊዎች ፍርድ ቤት ዋና ፎቅ ሪሴፕሽኒስት (206) 477-2902

የ court hearing (የፍርድ ቤት ችሎት) ከዳኛ ጋር የሚደረግ ስብሰባ ነው።

የታዳጊዎች የፍርድ ቤት ሂደት ከጥቂት ሳምንታት እስከ ብዙ ወራት ሊወስድ ይችላል። ለመታደም ብዙ ችሎቶች አሉ፣ እና በመርሐግብር እና በሌሎች ምክንያቶች ላይ በመመርኮዝ እነዚህ በሳምንታት ልዩነት ሊከናወኑ ይችላል። ልጅዎ ከተከሰሰበት ክስ ጋር እና የፍርድ ቤቱ ቀጣይ ቀን ደብዳቤ በፖስታ ይላክልዎታል። ፍርድ ቤቱ እና የህዝብ መከላከያ መምሪያ (DPD) እርስዎን ሊያገኙ የሚችሉበት የፖስታ አድራሻ መኖሩ በጣም አስፈላጊ ነው። ቋሚ አድራሻ ከሌለዎት የእጓደኛ ወይም የቤተሰብ አባል አድራሻ ይስጧቸው።

ልጅዎ ወደ እያንዳንዱ ችሎት መምጣት ካለበት የልጅዎን ተከላካይ ጠበቃ ይጠይቁ። የልጅዎ እዚያ መሆን የማያስፈልግ ከሆነ፣ የልጅዎ ተከላካይ ጠበቃ መገኘት ያለበትን ቀጣይ የፍርድ ቤት ቀን ይነግርዎታል። አብዛኛውን ጊዜ፣ የልጅዎ JPC ከችሎቱ ቀን ጋር በተመሳሳይ ጊዜ ስብሰባ ያዘጋጃል፣ ስለሆነም ቀጠሮ ስለመኖሩ ከልጅዎ የአመክሮ አማካሪ ያረጋግጡ።



የፍርድ ቤቱ ሂደት
1
የመጀመሪያ ችሎት
የመጀመሪያ ስብሰባ ከዳኛ ጋር
የአቃቤ ሕግ እና የተከላካይ ጠበቆች አቋማቸውን እና ለምን እንደሆነ ይናገራሉ
የወጣቶች መጠለያ
ደህንነቱ የተጠበቀ እስር ቤት
የኤሌክትሮኒክ ቁጥጥር
ተለቋል
ወላጅ፣ አሳዳጊ፣ ወይም ቤተሰብ
በልዩ ሁኔታዎች
አዎ
የፋይል ክፍያዎች
አይ
ወደ ቤት እንሂድ
ቀጣይ እርምጃዎች
ከ.... ጋር መገናኘት
ወይም
የኤሌክትሮኒክ ቁጥጥር ሰራተኞች ደህንነቱ ለተጠበቀ እስር አማራጭ
2
ክስ የመመስረቻ ችሎት
ዳኛው ልጅዎ በምን እንደተከሰሰ ይነግረዋል
ሊሆኑ የሚችሉ አንዳንድ አማራጮች
3
የጉዳይ ማቅረቢያ
በጉዳዩ ላይ ተወያዩ እና ልጅዎን ይምከሩ
ለመዘጋጀት ጉዳዩን ያስተላልፉ
ወደ ችሎት ይሂዱ
ጥፋተኛ ነኝ ብሎ መናገር
4
እውነታን ፍለጋ ችሎት
ወር
ለመሄድ ነፃ
ዳኛው ይወስናል
ጥፋተኛ አይደለም
ጥፋተኛ ነው
5
የተማጽኖ ችሎት
ዳኛው ብይን ይሰጣል
የአመክሮ ጊዜ
ካሳ $
የእስር ጊዜ

ሁሉም ሰው የተለየ ተሞክሮ ይኖረዋል፣ በተመሳሳይ የፍርድ ቤት ቀጠሮ አንዳንድ ጊዜ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ችሎቶች ይከሰታሉ። በሌሎች ጊዜያት፣ እያንዳንዱ ችሎት በተለየ ቀን ይሆናል። የተወሰኑት ችሎቶች የሚከሰቱት በፍርድ ቤት ክፍል ውስጥ ሲሆን አንዳንዶቹ ደግሞ በመጠበቂያ ክፍል ውስጥ ይሆናሉ። የፍርድ ቤት ችሎት በጣም በፍጥነት ሊካሄድ ስለሚችል፣ በኋላ ላይ የልጅዎን የመከላከያ ጠበቃ ወይም የመግቢያ የአመክሮ አማካሪ መጠየቅዎን ለማስታወስ ጥያቄዎችዎን መፃፍ ጥሩ ሀሳብ ነው።

## የመጀመሪያ ችሎት

First Hearings (የመጀመሪያ ችሎቶች) ልጅዎ ከታሰረ በኋላ ባለው የስራ ቀን ይከናወናል። Juvenile Probation Counselor ወይም የ Department of Public Defense ተከላካይ ጠበቃው ለችሎቱ መቼ መገኘት እንደሚችሉ ሊነግርዎት ይደውላል። በአካል የማይገኙ ከሆኑ በስልክ መቀላቀል ይችላሉ።

**በችሎቱ ወቅት** ከልጅዎ ጋር መነጋገር አይችሉም። የአቃቤ ሕግ ጠበቃ እና የልጅዎ ተከላካይ ጠበቃ ስልጣናቸው ምን እና ለምን እንደሆነ ለዳኛው ይነግሩታል። ዳኛው ከእርስዎ ለመስማት ሊጠይቅ ይችላል። መናገር ስለሚፈልጉት ነገር አስፈላጊ ነጥቦችን ፅፎ መዘጋጀት ጠቃሚ ነው። ቃላቶችዎ የበለጠ ኃይል እንዲኖራቸው አጭር ያድርጉት።

**በችሎቱ ላይ**፣ ዳኛው ልጅዎ እንደተለቀቀ ወይም በእስር ላይ እንደሚቆይ ይወስናል።ዳኛው ይህንን ውሳኔ የሚወስነው ልጅዎ በተከሰሰባቸው ክሶች፣ በልጅዎ ወይም በሌሎች ደህንነት ስጋት እና ከልጅዎ የህግ ስርዓት ታሪክ ጋር በመመስረት ነው። ዳኛው በልጅዎ ላይ ሊወስን የሚችለውን ውሳኔ የሚከተለው ነው፦

1. ዳኛው በልጅዎ ላይ የደህንነት ስጋት ካለበት፣ ወይም ልጅዎ በቀጣዩ ችሎት ቀን አይመጣም የሚል ስጋት ካለበት ልጅዎን ደህንነቱ በተጠበቀ እስር ቤት ይይዛሉ።
2. ልጅዎን ወደ ቤትዎ እንዲወስዱት ይለቃል
3. በእርስዎ ፈቃድ ለቤተሰብ አባል ይለቃል
4. "probable cause (ሊሆን የሚችልበት ምክንያት)" ካልተገኘ በስተቀር በተለዩ ሁኔታዎች ይለቀቃል (ለምሳሌ ወንጀል አለመፈፀም ወይም ከተወሰኑ ሰዎች ጋር ግንኙነት አለማድረግ)
5. ልጅዎ በቤትዎ ውስጥ መቆየቱን በተመለከተ የደህንነት ስጋት ካለብዎት ወደ የወጣት መጠለያ ተልኳል
6. የተለቀቀው በ Electronic Home Monitoring (EHM፣ **በኤሌክትሮኒክ የቤት ቁጥጥር**) ከቁርጭምጭሚት መሳሪያ ጋር

**ከችሎቱ በኋላ** ከ JPC ጋር እንዲገናኙ ይመራሉ ወይም ልጅዎ በኤሌክትሮኒክ የቤት ቁጥጥር እንዲደረግ ከተመደበ ከ EHM (ASD) ሰራተኞች ጋር ይገናኛሉ። ስለሚቀጥሉት እርምጃዎች ያነጋግሩዎታል። ወደ ችሎት ሌላ ጉዞ እንዳያደርጉ ከችሎቱ በኋላ ወዲያውኑ ከእነሱ ጋር መገናኘት ይሻላል። ከፍርድ ቤቱ ችሎት በኋላ ወዲያውኑ መሄድ ከፈለጉ፣ ቢያንስ ቀጠሮ ለመያዝ ከአመክሮ አማካሪው ወይም ከEHM ሰራተኞች የእውቂያ መረጃ ለማግኘት ይምጡ።እነሱ ይጠብቁዎታል።

አቃቤ ህጉ በልጅዎ ላይ ክስ መመስረታቸውን ይወስናል። ክሶችን የማያቀርቡ ከሆነ፣ እርስዎ እና ልጅዎ እንደገና ወደ ፍርድ ቤት መሄድ አያስፈልግዎትም። PAO ክስ እያቀረበ ከሆነ፣ ዳኛው በክሱ ችሎት ላይ ይነግርዎታል። በመጀመሪያ ችሎት ወቅት፣ አቃቤ ሕግ ክሱን ስለ መጫን ወይም ስለ "የችኮላ ክሶች" ቀናት ከዳኛው ጋር ሲነጋገር መስማት ይችላሉ።

# ተጨማሪ ችሎቶች

PAO ክስ ለመመስረት ከመረጠ፣ ልጅዎ ተጨማሪ**የችሎት ቀጠሮ**ይያዝለታል። ልጅዎ ሊገኝባቸው የሚችላቸው ችሎቶች የሚከተሉትን ያጠቃልላል፦

## ክስ መክሰስ

Arraignment (ክስ መክሰስ) ዳኛው ለልጅዎ አቃቤ ሕግ በምን እየከሰሳቸው እንደሆነ ሲነግሯቸው ነው። ለአነስተኛ ጥፋቶች፣ ከልጅዎ እና ከተከላካይ ጠበቃቸው ጋር በፍርድ ቤት አዳራሽ ውስጥ ክስ ይመሰረታል።በጣም ከባድ ለሆኑ ወንጀሎች፣ ክስ በፍርድ ቤቱ ውስጥ ይመሰረታል። ብዙ ሰዎች "ጥፋተኛ አይደለሁም" ይላሉ። የሚቀጥለው ችሎት፣ "የጉዳይ ማቅረቢያ ችሎት" ቀጠሮ ይያዝለታል።

## የጉዳይ ማቅረቢያ

የ Case Setting Hearing (የጉዳይ ማቅረቢያ ችሎት) በልጅዎ እና በተከላካይ ጠበቃቸው መካከል በፍርድ ቤት ማቆያ ክፍል ውስጥ የሚካሄድ ስብሰባ ነው።ተከላካይ ጠበቃው በስብሰባው ወቅት ከልጅዎን ለብቻው ሊያነጋግር ይችላል። የዚህ ስብሰባ ዓላማ ልጅዎ እና ተከላካዩ ጠበቃ በጉዳዩ ላይ እንዲወያዩ እና ተከላካዩ ጠበቃ ስለአማራጮች ለልጅዎ እንዲመክሩ እና ልጅዎ ምን ዓይነት ምርጫ ማድረግ እንዳለበት እንዲወስን ለመርዳት ነው።

ልጅዎ፣ በተከላካይ ጠበቃቸው እገዛ፣ ጥፋተኛ መሆኑን ለመናገር ወይም ችሎት ቀጠሮ ለማስያዝ ወይም ለተጨማሪ ዝግጅት ችሎቱን ለሌላ ጊዜ ማስተላለፍ ይወስናል። በዚህ ውሳኔ መሰረት የተከላካይ ጠበቃ የፍርድ ቀን፣ አዲስ የክስ ማቅረቢያ ቀን ወይም የይግባኝ ቀን ይመድባል።

የጉዳይ ማቅረቢያ ችሎቶች ብዙውን ጊዜ "የቀጠለ" ነው፣ ይህም በማንኛውም ወገን ሊጠየቅ ይችላል። በአብዛኞቹ ሁኔታዎች፣ ወጣቱን ወክሎ ተከላካዩ ቀጣይነቱን ይወስናል እናም ዳኛው ከተሰጠ ያዝዘዋል። "continuance (ቀጣይነት)"፣ ሲኖር እርስዎ እና ልጅዎ እዚያ መሆን አያስፈልግዎትም።

## ብቃት

"Competency (ብቃት)" ማለት ልጅዎ የፍርድ ቤቱን ሂደት ተረድቶ ተከላካይ ጠበቃቸው እንዲከላከልላቸው ማገዝ ይችላሉ ማለት ነው። የችሎታ ችሎት ዳኛው ልጅዎ ለፍርድ "ብቁ" መሆኑን ሲወስን የሚያዝ ነው። አንድ ልጅ ብቃት ከሌለው ለፍርድ ሊቀርብ አይችልም። ልጅዎ ብቃት ከሌለው፣ ብቃት እንዲኖረው ልጅዎ ወደ አእምሮ ሆስፒታል ሊላክ ይችላል። እንዲሁም ዳኛው ጉዳዩን ውድቅ ያደርጉ ይሆናል፣ ይህም ማለት ለፍርድ መቅረብ እና በልጅዎ ላይ ክስ አይኖርም።

## Omnibus(ኦምኒባስ)

ይህ ችሎት ለ "እውነታን ፍለጋ" ፍርድ ለመዘጋጀት ጥቅም ላይ ይውላል። ብዙውን ጊዜ ከችሎቱ በፊት ባለው ሳምንት ውስጥ ይካሄዳል። በዚህ ችሎት፣ አቃቤ ሕጉ እና የመከላከያ ጠበቃው ለፍርድ ለመቅረብ ዝግጁ መሆናቸውን ለዳኛው ይነግሩታል። ጠበቆቹ ለችሎቱ ለመዘጋጀት የበለጠ ማድረግ ካስፈላጋቸው፣ ዳኛው የፍርድ ሂደቱን ሊያዘገይ ይችላል። ጠበቆቹ ለፍርድ ዝግጁ ከሆኑ፣ ችሎቱን ለማካሄድ የሚያስችላቸውን መረጃ ለዳኛው ይሰጣሉ። ዳኛው የፍርድ ሂደቱ ከመቀጠሉ በፊት ውሳኔ የሚያስፈልጋቸውን ቀሪ ጉዳዮች ሊፈቱ ይችላሉ።

## ለፍርድ መቅረብ/እውነታን-የመፈለግ ችሎት

የ "Fact-Finding Hearing (እውነታ ፍለጋ ችሎት)" " ወይም Trial (ለፍርድ መቅረብ) ዳኛው ልጅዎ ጥፋተኛ መሆኑን ወይም ጥፋተኛ አለመሆኑን የሚወስንበት ችሎት ነው። በታዳጊዎች ፍርድ ቤት ውስጥ የፍርድ ሸንጎ አባላት የሉም፤ ውጤቱ የሚወሰነው በዳኛው ነው። ዳኛው ልጅዎ ጥፋተኛ መሆኑን ለመወሰን፣ አቃቤ ህጉ ጠበቃው ልጅዎ በወንጀል ጥፋተኛ መሆኑን ለ "beyond a reasonable doubt (ከተገቢ ጥርጣሬ በላይ)" የሆነን በቂ ማስረጃ ማቅረብ አለበት። ልጅዎ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ፣ የሚቀጥለው ችሎት "የማስወገጃ ችሎት" ይሆናል።

## የተማጽኖ ችሎት

እነዚህ ሁለት ችሎቶች አብዛኛውን ጊዜ የተዋሃዱ ናቸው። በ "Plea Hearing (ተማጽኖ ችሎት)"፣ ወቅት ወጣቱ እና ጠበቃው በመከላከያ እና በአቃቤ ህግ መካከል ድርድርና ስምምነት የተደረገባቸውን ትክክለኛ ክሶች ይቀርብላቸዋል። ከዚያ በኋላ ወጣቱ በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ መሆኑን ይናገራል።

በታዳጊዎች የሕግ ሥርዓት ውስጥ "Disposition (አፈፃፀም)" በአዋቂዎች ሥርዓት ውስጥ ከ "Sentencing (ፍርድ)" ጋር አንድ ነው። በ disposition hearing (አፈፃፀም ችሎቱ) ወቅት አቃቤ ህጉ፣ ተከላካይ ጠበቃው፣ እና JPCው እያንዳንዳቸው የውሳኔ ሃሳቦቻቸውን/ምክሮቻቸውን ያቀርባሉ። ወጣቶቹም፣ አሳዳጊ(ዎቹም) አስተያየታቸውን ይሰጣሉ። በመጨረሻም፣ ዳኛው በአፈፃፀም (ፍርዱ) ላይ ውሳኔ ይሰጣል።የአፈፃፀሙ ትእዛዝ የታዳጊዎችን የሕግ ሂደትን ልጅዎ በተሳካ ሁኔታ ለማጠናቀቅ ምን ማድረግ እንዳለበት ይገልጻል። ዳኛው ልጅዎ ተጠያቂነትን እንዲማር ይረዳሉ ብለው የሚያስቡትን፣ የህብረተሰቡን ደህንነት የሚጠብቅ እና ልጅዎን ባህሪን እንዲያሻሽል የሚረዳውን ይመለከታል/ከግምት ያስገባል። ምሳሌዎች የአመክሮ ጊዜን፣ የምክር አገልግሎትን፣ የማህበረሰብ አገልግሎትን፣ መመለስ (ገንዘብ መመለስ) እና የእስር ጊዜን ያካትታሉ። ልጅዎ በአፈፃፀም ትእዛዝ ውስጥ ያሉትን ህጎች የማይከተል ከሆነ፣ ልጅዎ ዳኛው ጋር እንደገና መቅረብ አለበት እና ተጨማሪ ቅጣቶችን ያዝዙ ይሆናል። የፍርድ ቤቱ ሰራተኞች ከአፈፃፀሙ ችሎት በኋላ የልጁን የአፈፃፀም ትዕዛዝ ቅጅ ይሰጡታል።

## ካሳ

ዳኛው ለልጅዎ restitution (ካሳ) እንዲከፍል (ለተፈፀመ ጥፋት ገንዘብ መክፈል)፣ ካዘዙ ዳኛው የካሳ ችሎት ቀጠሮ ሊይዙ ይችላሉ። ይህ ዳኛው ልጅዎ ምን ያህል ገንዘብ መክፈል እንዳለበት ሲወስን ነው። ፍርድ ቤቱ ልጅዎ ለመክፈል የሚያስፈልገውን ገንዘብ ለማግኘት የሚረዳ የስራ ፕሮግራሞች አሉት።

## ማሻሻያ

ልጅዎ የአመክሮ ጊዜውን ህግ የሚጥስ ከሆነ JPC ከዳኛው ጋር የ Modification hearing (የማሻሻያ ችሎት) ቀጠሮ ይይዛል። JPCው ስለ ልጅዎ የአፈፃፀም ትዕዛዝ ዳኛው ምን መለወጥ እንዳለበት ይመክራል።

## የእስር ግምገማ

በ Detention Review (በእስር ግምገማ) ወቅት ዳኛው የወጣቱን የጥበቃ ሁኔታ ይመለከታሉ።ወጣቱ/ተከላካዩ፣ አቃቤ ሕግ፣ ወይም JPC የወጣትን የእስር ሁኔታ ለመቀየር ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ። ዳኞች ወደ EHM፣ ወይም ደህንነቱ ወደ ተጠበቀ እስር ማዘዋወር ይችላሉ። በተገላቢጦሽ፣ ዳኛው ወጣቱን ደህንነቱ ከተጠበቀ እስር ወደ EHM ወይም ሙሉ በሙሉ እንዲለቀቅ ሊያደርግ ይችላል።

# ብዙም ያልተለመዱ ችሎቶች



## የብቃት ችሎት

- ልጅዎ የሚችል ከሆነ ዳኛ ይወስናል
  - [ ] ጉዳያቸውን መረዳት
  - [ ] የፍርድ ቤት ሂደቱን መረዳት
  - [ ] ጠበቃቸውን መርዳት

## የእስር ግምገማ

- ሁሉም ወገኖች ልጅዎ የሚከተሉትን ይባል እንደሆነ ለመወሰን አንድ ላይ ይመጣሉ
  - [ ] ወደ እስር ቤት መግባት
  - [ ] ከእስር ቤት መለቀቅ
  - [ ] የኤሌክትሮኒክ የቤት ቁጥጥርን ማድረግ ወይም ማውጣት

## ኦምኒባስ ችሎት



- ለእውነታን ፍለጋ ችሎት ጥቅም ላይ ይውላል
- አቃቤ ሕጉ እና ተከላካይ ጠበቃው እስር ቤት ለመግባት ዝግጁ መሆናቸውን ለዳኛው ይነግሩታል።

## Diversion (ብዝሃነት)

ፖሊስ ለ PAO ሪፈራል ካቀረበ፣ PAO ባህላዊውን የህግ መንገድ ከፍርድ ቤቱ ጋር ለመከተል ወይም ልጅዎን ወደ ተለዋጭ መርሃግብር እንዲወስን ይወስናል። እነዚህ አማራጭ መርሃግብሮች ወጣቶች ለባህሪያቸው እና ለድርጊታቸው ሃላፊነትን እንዲወስዱ በማድረግ የባህሪያቸውን መሰረታዊ ችግሮችን በመንቀፍ እና በማህበረሰባቸው እንዲቆዩ ያደርጋል። መርሃግብሮቹ ከማህበራዊ ድርጅቶች እና ግለሰቦች ጋር በመቀናጀት ለታዳጊዎች እና ለወጣቶች ድጋፍን ያደርጋል።

መርሃግብሮቹ አብዛኛውን ጊዜ ቀለል ላለ ወንጀል ለሰሩ የተዘጋጀ ቢሆንም ኪንግ ካውንቲ ከባድ ወንጀል ለፈጸሙም ታዳጊዎች እንዲዳረስ ጥረት እያደረገ ይገኛል። ከስር የተዘረዘሩት በምሳሌነት ይጠቀሳሉ።

**Family Intervention and Restorative Services (FIRS፣ የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት እና መልሶ ማቋቋሚያ አገልግሎቶች)** – የማገገሚያ ስብሰባዎችን የሚያመቻች እና በታዳጊዎች የቤት ውስጥ ጥቃት ከተጎዱ ቤተሰቦች ግር በመገናኘት የማማከር እድልን የሚያቀርብ መርሃግብር ነው። የቤተሰቦቻቸው ደህንነት ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ለቤተሰቦች የማረፍያ ማዕከል ቀርቧል። ለበለጠ መረጃ ገጽ 11 ን ይመልከቱ።

**Juvenile Probation Counselor Diversion(የታዳጊዎች አመክሮ አማካሪ አቅጣጫ ለውጥ)** – አንዳንድ ጊዜ ታራሚው ለአቅጣጫ ለውጥ (Diversion) ብቁ በሚሆንበት ጊዜ PAO ወይም JPCው ታዳጊው በግለሰባዊ መርሃግብሮች ወይም የባህሪ ጤና ጣልቃ ገብነት ላይ በስኬት ከተሳትፉ ክሱ እንዲነሳላቸው ማድረግ እንዲችሉ ያደራድራል።

**Community Accountability Boards (CABs)(የማህበረሰብ ተጠያቂነት ቦርድ)** –CABs ትብለው የሚጠሩት የታዳጊ ወጣቶችን ቀላል ፍርድ ከቤተሰብ እና ከታራሚዎች ጋር በመሆን ለማስፈፀም እቅድ የሚያወጡ የማህበረሰብ በጎ ፈቃደኞች ናቸው። **Choose 180** – የማህበረሰብ ድርጅት ሲሆን ቅድመ-አቅጣጫ ለውጥ፣ የግማሽ ቀን ወርክ ሾፕን በማዘጋጀት ታዳጊዎችን ከታዳጊዎች የህግ ስርዓት ለመታደግ እርዳታን እና እገዛን ያደርጋሉ። ወርክ ሾፑ በተሳካ ሁኔታ ከተጠናቀቀ ተሳታፊዎች ከህጋዊ የመሰናበቻ ሪፈራል አላቸው።

# ደጋፊ የፍርድ ቤት ፕሮግራሞች እና ጥምረቶች

የኪንግ ካውንቲ የታዳጊዎች የፍርድ ቤት አገልግሎት ከብዙ የማህበረሰብ ድርጅቶች እና የማህበረሰቡ አባላቶች ጋር የድጋፍ፣ የጣልቃ ገብነት እና የምክክር አገልግሎቶችን ይሰጣል። የዚህ ሥራ ጥልቅነት በማገገሚያ መርሆዎች ላይ የተመሠረተ ነው ፣ ይህም በማኅበረሰብ ውስጥ የሚደርሰውን ጉዳት በመጠገን እና መልሶ የመገንባትን አስፈላጊነት አስረግጦ ይቀበላል። ይህ ለወጣቶች ስነምግባር ምን ያህል ምላሽ ትኩረትን እና ልምዶችን ለመምራት እንደ እሴቶች ስብስብ ሆኖ ያገለግላል። በፍርድ ቤት የተሳተፉ ወጣቶችን ከማህበረሰቡ ጋር ተገናኝተው እንዲሳተፉ ለመርዳት የማህበረሰብ አጋርነቶች እና ፕሮግራሞች አስፈላጊ ናቸው። ከታዳጊዎች ፍርድ ቤት ጋር አብሮ ለመስራት እባክዎ የማህበረሰብ አጋር አስተባባሪውን ሮበርት ግራንትን በዚህ ያግኙ (206) 477-0041 rgant@kingcounty.gov

የ Youth Support Resources (የወጣቶች እርዳታ ግብዓት) በኪንግ ካውንቲ ለሚገኙ ወጣቶች እና ቤተሰቦች መረጃ እና ግብዓትን ያቀርባል። ግብዓቶቹ በአገልግሎት ዓይነት ፣ በእድሜ እና በተፈለገው የጉዞ ርቀት ሊከፋፈሉ ይችላሉ። የወጣቶች እርዳታ ግብዓትን ለባግኘት ይህንን ይጫኑ. ግብዓት ለማሻሻል ወይም መረጃን ለመስጠት በሚከተለው ኢሜል አድራሻ ይጻፉልን SCResourceCenter@kingcounty.gov.

## [Behavioral Health Response (BHR፣ የባህርይ ጤና ምላሽ)፦]

Behavioral Health Response (BHR፣ የባህርይ ጤና ምላሽ)፦የከፍተኛ ፍርድ ቤት ትራንስፎርሜሽናል BHR አጋርነት ግብ በከባድ ወንጀል የተከሰሱ ወይም BHR መደበኛ የመለየት ዝንባሌ ያላቸውን የወጣቶች ባህሪ ጤና (የአሰቃቂ የአእምሮ ታሪክ እና የሁለትዮሽ ምርመራ) መመርመር እና ማገልገል ነው ። በዚህ መንገድ ታራሚው ወጣት በታዳጊ አመክሮ አማካሪ (JPC) እና የማህበረሰብ መሪ ይታገዛል። ተሳታፊ ታዳጊዎች የተከሰሱበትን ወንጀል ወደ ቀላል ወንጀል ክስ ማቅለል ይችላሉ፡በተጨማሪም በስኬት ባጠናቀቁ ጊዜ ውሳኔዎቻቸውን የማስተለለፍ ወይም የመሰናበት አማራጭ ይቀርብላቸዋል። ምክንያቱም ይህ መንገድ ለማህበረሰብ ዝንባሌ እና የፍርድ ቅነሳ ስለሚሰጥ አቃቤ ህጉ ለዚህ መርሃግብር ብቁ የሆኑ ወጣቶችን በመለየት ይሳተፋል።

## [Aggression Replacement Training (ART) (የአመፅ መተኪያ ሥልጠና)] (206) 477-9573

የተሳታፊዎችን የእርስ በእርስ ፣ ስሜታዊ አያያዝ እና የባህሪ ክህሎትን የሚያሰፋ በፍርድ ቤት የቀረበው መርሃግብር ነው። ክህሎትን ማዳበር፣ ንዴትን መቆጣር እና የሞራል ብቃትን መሰረት ያደረጉ ሶስት ክፍል ያለው ካሪኩለምንም ይይዛል። ለ 10 ሳምንታት በሳምንት ሶስቴ፣ በቀን ለ 1 ሰዓት በድምሩ ለ 30 ሰዓት የሚሆን ይሆናል።

## [At Risk Youth (ARY፣ በስጋት ላይ ያሉ ወጣቶች)፣ Child In Need of Services (CHINS፣ አገልግሎት የሚያስፈልጋቸው ሕፃናት)፣ and Truancy Programs(ያለፍቃድ ከትምህርት ቤት የመቅረት ፕሮግራሞች)]

እነዚህ መርሃግብሮች በቤተሰብ ፍርድ ቤት የሚተዳደሩ ሲሆኑ ከአመክሮ በተለየ የከፍተኛው ፍርድ ቤት አካል ናቸው። የARY/CHINS መርሃግብሮች ስለልጃቸው ባህሪ እና ደህንነት የሚጨነቁ እና የልጃቸውን ደህንነት ለመጠበቅ ከፍርድ ቤቱ እርዳታ ለማግኘት የሚፈልጉ ወላጆችን የሚረዳ ነው። ያለፍቃድ ከትምህርት ቤት የመቅረት መርሃግብር በትምህርት ቤቶች ወረዳ የተጀመረ ሲሆን ከታዳጊ ቤተሰቦች ጋር በመተባበር የልጆቻቸውን የትምህርት ግብን መሰረት ያደረገ የትምህርት እቅድን ያወጣል።

### At Risk Youth Petition (ARY፣ <u>በስጋት ላይ ያሉ ወጣቶች</u> አቤቱታ):

አንድ ወላጅ/አሳዳጊ የልጁን እንክብካቤ ፣ አሳዳጊነት እና ቁጥጥርን ለመጠበቅ እና በቤተሰብ መካከል የተፈጠረውን አለመግባባት ለመቅረፍ ከፍርድ ቤቱ ድጋፍ ለማግኘት የ ARY አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ። ፍርድቤቱ ታዳጊውን የማዘዝ እና የአገልግሎቶች ተካፋይ እንዲሆን ማዘዝ ይችላል። ጉዳይ አስተዳዳሪዎች ቤተሰቦችን ይደግፋሉ እንዲሁም እርቅን የሚያጠናክሩ መርሃግብሮችን ይጠቁማሉ። ሂደቱን ለመጀመር ወላጅ/አሳዳጊ Family Assessment (የቤተሰብ ምዘና) ከታዳጊ ልጆች እና ቤተሰቦች መምሪያ በ (800) 609-8764 ማግኘት ይኖርበታል።

ለበለጠ መርጃ የጉዳይ ሥራ አስኪያጁን በሚከተለው አድራሻ ያግኙ [https://www.kingcounty.gov/courts/superior-court/becca/ary.aspx]፦

King County Courthouse in Seattle – የጉዳይ ሥራ አስኪያጅ (206) 477-4946
Serves Bellevue, Issaquah, Lake Washington, Mercer Island, Northshore, Riverview, Seattle, Shoreline, Skykomish, Snoqualmie, & Vashon school districts

Maleng Regional Justice Center in Kent - የጉዳይ ሥራ አስኪያጅ (206) 477-2759
Serves Auburn, Enumclaw, Federal Way, Highline, Kent, Renton, Tahoma, & Tukwila school districts

**Child in Need of Services (CHINS፣ አገልግሎት የሚያስፈልጋቸው ሕፃናት)**

A CHINS አቤቱታ በውላጅ/በአሳዳጊ፣ በታዳጊ DCYF ሊሞላ ይችላል። ታዳጊው በቤት ውስጥ በሚኖርበት ጊዜ ሊፈታ የማይችል ከባድ ግጭት ካለ ፣ ቤተሰቡ እንደገና ለመገናኘት በሚሠራበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ ለ 6 ወራት ጊዜያዊ ከቤት ውጭ ምደባን ሊፈቅድ ይችላል።

ሂደቱን ለመጀመር ወላጅ/አሳዳጊ Family Assessment (የቤተሰብ ምዘና) ከታዳጊ ልጆች እና ቤተሰቦች መምሪያ በ (800) 609-8764 ማግኘት ይኖርበታል።

ለበለጠ መርጃ የጉዳይ ሥራ አስኪያጁን በሚከተለው አድራሻ ያግኙ https://www.kingcounty.gov/courts/superior-court/becca/chins.aspx:

King County Courthouse in Seattle – የጉዳይ ሥራ አስኪያጅ (206) 477-4946
Serves Bellevue, Issaquah, Lake Washington, Mercer Island, Northshore, Riverview, Seattle, Shoreline, Skykomish, Snoqualmie, & Vashon school districts

Maleng Regional Justice Center in Kent - የጉዳይ ሥራ አስኪያጅ (206) 477-2759
Serves Auburn, Enumclaw, Federal Way, Highline, Kent, Renton, Tahoma, & Tukwila school districts

## Truancy & Education Reengagement (ያለፍቃድ ከትምህርት ቤት መቅረት እና ትምህርትን እንደገና ማደስ)

በዋሽንግተን ግዛት በህግ "Truancy Petition (ያለፍቃድ ከትምህርት ቤት የመቅረት አቤቱታን)" ማቅረብ የሚገባቸው በአንድ ወር ውስጥ ከሰባተኛው ያለፍቃድ ቀሪ ወይም በአንድ አመት ውስጥ ከአስረኛው ቀሪ በፊት መሆን ይኖርበታል። (RCW 28A.225.030). Truancy Petition (አውቆ ቀሮችን የማስቆም አቤቱታ) አውቆ ቀሮችን የማስቆም አቤቱታ የሲቪል አቤቱታ ሲሆን ትምህርት ቤቶች ትማሪዎችን መልሰው ወደ ትምህርት ቤት የመመለስ አቤቱታ ነው። ትምህርት ቤቶች በወረዳዎቻቸው ላይ ያለፈቃድ መቅረትን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚረዱ ጣልቃ ገብነቶችን እንዲያደርጉ ህጉ ያስገድዳል።

በኪንግ ካውንቲ የያለፍቃድ ከትምህርት ቤት መቅረት እና ትምህርትን እንደገና ማደስ ግብ ከወረዳ ትምህርት ቤቶች ጋር መስራት እና ታዳጊዎች በትምህርት እንዲዳብሩ ለቤተሰቦች የትምህርት ቤት የመቀረትን እንቅፋት ማንሳት ይሆናል። ፍርድ ቤቱ ታዳጊው ወደ ፍርድ ቤት በትምህርት ገበታ ላይ ያለፈቃድ ባለመገኘት ቢቤቱታ መሰረት ወደ ፍርድ ቤቱ መምጣት ካለበት ይወስናል። የፍርድ ቤት ችሎት ከመቅረቡ በፊት ታዳጊዎች እና ቤተሰቦች እንደገና ለመግባት፣ አጠቃላይ እና መልሶ የማቋቋም ዘዴን ለመከትል ወደ በርካታ የህብረተሰብ ድጋፎች ይጋበዛሉ። የትምህርት ማሻሻያ ቡድን ወጣቶችን ከመደበኛ የፍርድ ቤት የፍርድ ሂደት በማሳደግ በማህበረሰብ አጋርነቶች ፣ በትምህርት መልሶ ማጎልበት ወርክሾፖች ፣ በቅድመ-ችሎት ስብሰባዎች ፣ በአስተማሪነት ፣ በወጣት ተሟጋቾች ፣ በማህበረሰብ ስብስቦች እና በአማራጭ የትምህርት መርሃ ግብሮች አማካይነት አዎንታዊ ውጤቶችን ለማግኘት ይጥራል። ከትምህርት ቤት ያለ ፈቃድ መቅረት በወረዳ ደረጃ የማህበረሰብ የሥራ ማቆያ ቦርድ ይስተናገዱሉ።

**የኪንግ ካውንቲ ቤካ የፍርድቤት አስተባባሪ፦** (206) 477-2746

**የኪንግ ካውንቲ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የታዳጊዎች ክፍል** (206) 477-2746

የበለጠ ለማወቅ የትምህርት ቤትዎን ወረዳ ማነጋገር እና የወረዳዎን የሥራ ማጣት መረጃ እዚህ ማግኘት ይችላሉ

https://www.k12.wa.us/student-success/support-programs/attendance-chronic-absenteeism-and-truancy/district-truancy-liaison

**የወረዳው ተወካዮች የግንኙነት መረጃ:-** https://www.k12.wa.us/student-success/support-programs/attendance-chronic-absenteeism-and-truancy/district-truancy-liaison

**ምክትል አቃቤ ህግ:-** Desk (206) 477-4336 | Cell (206) 965-5614

**አማራጭ የትምህርት እድል እየፈለጉ ነው?** ከእድሎ ጋር መልሰው ይገናኙ: [https://reopp.org/](https://reopp.org/)

## [የታዳጊዎች የፍትህ ምዘና ቡድን](#) (206) 263-1522

Juvenile Justice Assessment Team (JJAT፣ **የታዳጊዎች የፍትህ ምዘና ቡድን**) ከፍርድ ቤት ጋር ግንኙነት ያላቸውን ታዳጊዎች በማግዝ በአይምሮ ጤና፣ አደንዛዥ እጽ እና የሳይኮሎጂ ምዘናዎችን እና ማማከርን ዕቅድ በማውጣት ይረዳል። JJAT ከማህበራዊ የባህሪ ጤና አጋሮች ጋር በጋራ ከ([Ryther](#) and [Seneca Family of Agencies](#)) እና ኪንግ ከውንቲ የታዳጊዎች ፍርድ ቤት ጋር አብሮ ይሰራል። Ryther እና Seneca የክሊናል ምዘናን የሚሰሩ የኮንትራት ሰራተኞችን ያዘጋጃል።

JJAT የልሊኒካዊ የሥነ-ልቦና ባለሙያዎችን ማለትም የክሊኒካል ሳይኮሎጊስቶችን፣ የአእምሮ ጤና ባለሞያዎችን፣ የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀም ጋር የተያያዙ የመረበሽ ስሜቶችን የሚያክሙ ባለሙያዎችን ጨምሮ የተለያዩ ምክር ሰጪ ባለሙያዎችን ቡድን ያጠቃልላል። የ JJAT ቡድን የ JJAT ን ተቆጣጣሪ, የመርሃግብር አስተባባሪን እና የቤተሰብ አጋሮችን ያጠቃልላል። JJAT የወጣቶችን ወቅታዊ ፍላጎቶች ሙሉ ግንዛቤ ለማግኘት፣ ምዘናውን የሚያከሂዱት ባለሙያዎች በቻሉት መጠን በቢሮ ፣ በማህበረሰብ ወይም ክእስረኞች ጋር ብዙ ጊዜ ይገናኛሉ

## የበላይ ፍርድ ቤት የልጆች እና የቤተሰብ መርጃ/ሀብት ማዕከል

ለወጣቶች ማህበረሰብን ማዕከል ያደረጉ ትርጉም ሚሰጡ ግንኙነቶች ለስኬታቸው ወሳኝ ናቸው። የBobbe J. Bridge የመረጃ/ግብዓት ማዕከል ታዳጊዎች እና ቤተሰቦች ጠቃሚ እና የሚረዱ ለመረጃ፣ መርሃግብሮች እና እድሎች ትደራሽነትን ማስፋፋት ነው። የBobbe J. Bridge የመረጃ/ግብዓት ማዕከል በበጎ ፈቃድ የተመሰረተ፣ በመካከለኛ ቦታ በልጆችና በቤተሰብ ላይ የተቀናጀን ድጋፍ የሚያደርግ ነው። የመረጃ/ግብዓት ማዕከል ከሰኞ እስከ አርብ ከ8:30 AM እስከ 4:30PM ሰዓት ላይ ናቸው። ማንኛውም ሰው በዚህ ሰዓት መጥቶ አግልግሎት ማግኘት ይቻላል። ለማግኘት በዚህ ቁጥር ይደውሉ (206) 263-8634.

የግብዓት ማዕከል **Clothing Shop (የልብስ ሱቅ)** ታዳጊዎች ወደ ሥራ ቃለ መጠይቅ ሲሄዱ ፣ ፍርድ ቤት ሲቀርቡ፣ የሽልማት ሥነ ሥርዓት፣ የምረቃ ወይም ሌላ ልዩ ዝግጅት ላይ ሲገኙ በነፃ፣ በጥሩ ሁኔታ የተያዙ ፣ አዲስ ወይም ያገለገሉ የልብስ እና የመዋቢያ ቡቲክ መሰል ልብስ ሱቆች ይጋኛሉ። ስለ ለበለጠ መረጃ The Clothing Shop [ይህንን ይጫኑ](#)

## Juvenile Court Education and Employment Training (የታዳጊዎች ፍርድቤት ትምህርት እና ስራ ቀጠራ ስልጠና) (206) 477-3020

Education and Employment Training (EET፣ ትምህርት እና የስራ-ቅጥር ስልጠና) ለትምህርት ስኬት፣ የስራ ዝግጅት፣ ስልጠና እና የሚያበቃ የፍርድ በቤት ጣልቃ-ገብነት ተመስርቶ እርዳታን ያደርጋል። EET ከፍርድ ቤት ጋር የተያያዙ እድሜያቸው ከ 15-19 የሆኑ ታዳጊ ወጣቶችን የትምህርት እና የስራ ቅጥር ላይ ስኬታማ እንዲሆኑ ይረዳቸዋል። በኪንግ ካውንቲ ከሚገኙ ታዳጊዎች ጋር አብረው የሚሰሩ የትምህርት እና የስራ-ቅጥር ስፔሻሊስቶች። EET ሪፈራሎችን ይቀበ። እንዲሁም የወጣቶች ጋር አሙቱን ሙሉ ይሰራል።

EETን ለመመዝገብ ወይም ወደ EET ሪፈር ለመደረግ ፍላጎት ካለዎት ብቁነትዎን ለመገምገም እባክዎ የተመደበሎትን የታዳጊዎች አመክሮ አማካሪዎን ያነጋግሩ።

# እስርን የማስጠበቅ አማራጮች፦

**<u>ኤሌክትሮኒክ የቤት ውስጥ ክትትል (206) 477-9915 or (206) 477-9891</u>**

ፍርድ ቤቱ ልጅዎ ወደ ፍርድ ቤት እንዳይመለስ ሲጨነቅ ፣ እና ልጅዎ ከእስር ውጭ የሚፈልገውን ድጋፍ ማግኘት እንደሚችል ፍርድ ቤቱ ልጅዎን በኤሌክትሮኒክ የቤት ቁጥጥር (ኢኤችኤም) ላይ ሊያደርገው ይችላል ። DAJD ያሉበትን በጣ እንዲቆጣጠር የEHM ቁርጭምጭሚት ብራስሌት ይሰጣቸዋል። ይህ አማራጭ ልጅዎ ደህንነቱ በተጠበቀ እስር ቤት ከመሆን ይልቅ በቤቱ እና በማህበረሰቡ ውስጥ እንዲኖር ያስችለዋል።

ልግዎ የEHM መርሃ ግብር አካል ከሆነ የDAJDን ሰራተኛ ይተዋወቃሉ። ሰራተኞቹ ልጅዎን ከ EM ጋር ለማቀናበር የሚረዱ የምደባ ባለሙያዎችን እና ከዚያም የማህበረሰብ ቁጥጥር መኮንኖችን ያጠቃልላሉ ፣ ወጣቶች በ EHM ላይ የፍርድ ቤት ህጎችን እየተከተሉ መሆናቸውን እና በማህበረሰቡ ውስጥ ስኬታማ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ። ወጣቶች በ EHM ላይ እያሉ መሄድ የሚችሉት ወደ ቅድመ-ፀደቁ አካባቢዎች ብቻ እንደ ትምህርት ቤት ፣ የህክምና ወይም የምክር ቀጠሮዎች ፣ የፍርድ ቤት ችሎት ወይም የ JPC ወይም የጠበቃ ሹመቶች ብቻ ነው። የልጅ የጊዜ ሰሌዳ በDAJD ሰራተኛ መጽደቅ ይኖርበታል።

**<u>የቡድን እንክብካቤ</u>**

Group Care (የቡድን እንክብካቤ) የ24 ሰዓት የልጅዎ ጊዜያዊ የመኖሪያ አድራሻ ነው። ይህ መርሃግብር ማህበረሰብን ባማከለ ድርጅት ይመራል። ለምሳሌ YouthCare. የቡድን እንክብካቤ ከ 13-17 ባለው ዕድሜ ውስጥ ለሚገኙ ወጣቶች ይሰጣል። እንዲሁም ታዳጊው ልጅዎ በቡድን ቤቱ ውስጥ በሚቆይበት ጊዜ በሁሉም መርሃግብሮች ለመሳተፍ መስማማት ይኖርበታል። በቡድን ቤት ውስጥ በሚኖሩበት ጊዜ ልጅዎ በኤሌክትሮኒክ የቤት ቁጥጥር ላይ እንዲቀመጥ ማድረግ ይቻላል። የልጅዎ የተከሰሰበት ደረጃ እና በቡድን እንክብካቤ ውስጥ በሚቆዩበት ጊዜ ያለፉት ባህሪዎች በዚህ ፕሮግራም ውስጥ የመቀመጥ ችሎታ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ።

# መዝገቦችን መመለስ

በዋሽንግተን ግዛት ማንኛውም የታዳጊዎች የፍርድ ቤት ጉዳይ ለህዝብ ክፍት ነው። ይህ ማለት በልጆዎ ላይ የተመሰረተ ክስ ለህዝብ ክፍት ነው ማለት ነው። አንድ ታዳጊ ህጻን ወንጀለኛ ተብሎ በፍርድ ቤቱ ሲበየን “Adjudication (የፍርድ ቤት ፍርድ)”, የጥፋተኝነት ፍርድ ነው ማለት አይደለም። ሆኖም ግን Adjudication (የፍርድ ቤት ፍርድ) ለልጅዎ ስራ ለማግኘት ሊያከብድበት/ሊያከብድባት ይችላል። በልጅዎ የጥፋት ታሪክ ተመርኩዞ ልጅዎ ፍርዱን "ሊያዘጋ" ይችላል። ይህ ማለት የወደፊት ቀጣሪዎቹ/ቀጣሪዎቿ የልጅዎን መዝገብ ሊያዩ አይችሉም ማለት ነው። መዝገቡን ለማዘጋት ልጅዎ ለፍርድ ቤቱ ጥያቄን ማቅረብ አለበት። ስለ መዝገብ ማዘጋት የበለጠ ለማወቅ ከፈለጉ፣ ኪንግ ካዉንቲ Department of Defense ን በ (206) 296-7662 ማግኘት ይችላሉ።

ስለመዝገብ ማዘጋት የህግ አማካሪዎን እና JPCን ማነጋገሮ ይመከራል።

# ብዙ ጊዜ የሚያገለግሉ ቃላት

Adjudication (**የፍርድ ቤት ፍርድ**) ፍርድ ቤቱ አንድን ታዳጊ ጥፋተኛ ነው ሲል የሚሰጠው ብይን

Advocate (**ሞጋች**) በህግ ሙያ የሰለጠነና በሚመለከተው የህግ አካል የህግ ምክር ለመስጠት ወይም በፍርድ ክርክር ሌሎችን ወክሎ ችሎት ፊት ለመቆም ተገቢው ፈቃድ የተሰጠው ሰው።

Anger Replacement Training (**ብስጭትን ማብረጃ ስልጠና**) ታዳጊዎች ንዴታቸውን ትቆጣጥረው በአግባቡ ስሜታቸውን እንዲያስተዳድሩ እና እንዲግባቡ የሚያደርግ መርሃግብር ነው፡ በJPC እና በጤና አጋልግሎት ድርጅት አስተማሪነት የሚሰጥ ነው።

Arrested (**እስር**) አንድ ህጻን ወይም ታዳጊ በፖሊስ ቁጥጥር ስር ሲውል።

Arraignment (**አሬይንመት/ክስ መከሰስ**) ተከሳሽ ታዳጊው የሚለይበት፣ የክስ ዝርዝር/ ቻርጅ በመደበኛነት የሚነበብበት እንዲሁም ተከሳሹ ጥፋተኛ መሆኑ ወይም ያለመሆኑን ቃል የሚሰጥበት የፍርድ ቤት ሒደት።

Assessment (**ምዘና**) በባለሙያ የሚሰራ የታዳጊውን ፍላጎት ለማሟላት/ያላቸውን ችሎታ ማወቅ/ማግኘት የሚደረግ ቃለ ምልልስ።

At Risk Youth Petition (**አደጋ ላይ ላለ ታዳጊ ልጅ የሚቀርብ አቤቱታ**) አንድ ወላጅ/አሳዳጊ የልጁን እንክብካቤ ፣ አሳዳጊነት እና ቁጥጥርን ለመጠበቅ እና በቤተሰብ መካከል የተፈጠረውን አለመግባባት ለመቅረፍ ከፍርድ ቤቱ ድጋፍ ለማግኘት አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ።.

Attorney (**ጠበቃ**) or ነገረ-ፈጅ, የሰለጠነ እና ህጋዊ ፈቃድ ያለው የህግ ባለሙያ።

Case Manager (**ጉዳይ አስተዳዳሪ**) **ምዘናን፣ የደንበኛን እገዛ፣ እቅድ፣ ሙግት፣ እቅድ ማውጣትን፣ ሪፈራል እና የአገልግሎቶች ቅንጅትን የሚያቀርብ ይሆናል።**

Charge (**ክስ**) ታዳጊው ልጅ ህግን እንደተላለፈ የሚገልጸ ክስ።

Children and Family Justice Center (**የልጆች እና የቤተሰብ የፍትህ ማዕከል**) Building on 1211 E. Alder Street out of which የቤተሰብ ፍርድ ቤት አለልግሎቶች፣ የታዳጊዎች ፍርድ ቤት የ PAO ፣ የማህበረሰብ መርሃግብሮች የ FIRS ማዕከል እንዲሁም የታዳጊዎች ማረሚያ ይካተታሉ።

Child in Need of Services (**አገልግሎት የሚያስፈልጋቸው ህጻናቶች**) የህዝብ ሂደት በቤተሰብ፣ በታዳጊው ወይም በ DCYF ተወካይ የሚቀርብ አቤቱታ ሲሆን ጥያቄው ታዳጊውን አሁን ካለበት ቦታ ጠንከር ባለ ግጭት ምክንያት ወደ ሌላ ቦታ እንዲዘዋወር ይጠይቃል።

Child Protective Services (**የልጆች ጥበቃ አገልግሎት**) ለአደጋ ተጋላጭ ለሆኑ ፣ በቸልተኝናት ለተያዙ፣ ለአካላዊ ፣ ወሲባዊ ወይም ስሜታዊ ጥቃት የተጋለጡን ሕፃናት ጥበቃ የሚሰጥ የዋሽንግተን ግዛት የሕፃናት እና የቤተሰብ አገልግሎቶች መምሪያ ነው። ትኩረቱ በታዳጊ ልጁ/ልጅቷ ደህንነት ላይ እንዲሁም ቤተሰቦችን የማጠናከር እና ደህንነቱ የተጠበቀ የልጆች አስተዳደግን የሚያበረታታ ድጋፍ ነው።

Civil (**ሲቪል**) ለፍርድ ቤት የሚቀርብ አቤቱታ ሲሆን አንድ የቤተሰብ አባል ለሌላው የቤተሰብ አባል (በአሳዳጊ እና ለጆች ወይም ወጣቶች) የሚጋባውን ህጋዊ ግዳጅ እንዳልተወጣ የሚከስ ነው።

Community Accountability Boards (**የማህበረሰብ ተጠያቂነት ቦርድ**) \ታዳጊ ወጣቶችን ቀላል ፍርድ ከቤተሰብ እና ከታራሚዎች ጋር በመሆን ለመፈፀም እቅድ የሚያወጡ የማህበረሰብ በጎ ፈቃደኞች ናቸው።

**Community Empowerment Disposition Alternative Resolution (ማህበረሰብን የማጠናከር ሥርዓት አማራጭ)** ወጣቶች በወንጀል ከተከሰሱ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ከህብረተሰቡ ግብዓቶች እና ድጋፎች ጋር የሚያገናኝ መርሃግብር ነው። በመሳተፍ ታዳጊው እስርን ሊያስቀሩ ይችላሉ።

**Conditions of Probation (የአመክሮ ሁኔታዎች)** በዳኛው እምነት መሰረት ከ አንድ ታራሚ ወጣት ለሌላው ሊለይ ይችላል። የተለመዱ የአመክሮ ሁኔታዎች ትምህርት ቤትን መከታተል ፣ የቤት መርሆችን ማክበር እና ህገ-ወጥ የሆኑ እጾችን ማስወገድን ያካትታሉ። አንዳንድ ጊዜ ዳኛው የምክር ወይም የአደንዛዥ ዕፅ ሕክምና ፣ የማህበረሰብ አገልግሎት ወይም ተመላሽ ገንዘብ ሊያዙ ይችላሉ።

**Continuance (ቀጠሮ)** የፍርድ ቤት ሂደት ለቀጣይ ጊዜ ሲተላለፍ ወይም ሲራዘም።

**Counsel (ካውንስል)** ለተሟጋች ወይም ለጠበቃ ሌላ መጠሪያ።

**Court (ፍርድ ቤት)** በኪንግ ካውንቲ የሚገኘውን ከፍተኛ ፍርድቤትን በተለይም የታዳጊዎችን ክፍል ያመለክታል። የታዳጊዎችም ፍርድቤት በመባል ይታወቃል።

**Court Order (የፍርድ ቤት ትዕዛዝ)** በፍርድ አካል (በዳኛው) የሚሰጥ መደበኛ የጽሁፍ ትዕዛዝ ወይም የፍርድ ቤት ውሳኔ.

**De-Identification (ማንነትን መለየት)** የአንድን ሰውን ማንነት ካለው መረጃ ጋር በማነጣጠል የግለሰቡን ማንነት መጠበቅ።

**Department of Children, Youth, and Family Services (የልጆች፣ ታዳጊዎች እና ቤተሰብ አገልግሎት ክፍል)** በዋሽንግተን ግዛት ውስጥ የሚገኝ የመንግስት ኤጀንሲ ሲሆን ለህጻናት እና ለወጣቶች ደህንነት ኃላፊነት፣ ለቤተሰቦች ድጋፍ እና የህፃናት ደህንነትን የሚያረጋግጡ አገልግሎቶችን የሚያግዝ እቅድ ያወጣል።

**Dependency (ጥገኝነት)** የልጆችን ከለላ የሚዳስስ ሂደት ነው።

**Detained (መታሰር)** በእስር ቤት መያዝ።

**Disposition (የመጨረሻ ውሳኔ)** የፍርድ ቤት ዳኛው የወንጀል ክስን ሰምቶ በሚመለከተው ታዳጊ ላይ የሚሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ።

**Diversion (ብዝሃነት)** ከመደበኛ የፍትህ ስርዓት ወጭ በተለየ መንገድ የታዳጊውን ክስ የመመልከቻ እድል።

**Due Process (ሕግን ማስከበር)** ፍርድ ቤቶች አግባብ ያለው እና ፍትሃዊ ሂደቶችን መከተል ይኖርባቸዋል። ለምሳሌ፡ ለታዳጊዎች የፍርድ ቤት መቅረቢያ ቀናቸውን እና የእነሱን ምስክርነት ማድመጥ ይጋባቸዋል።

**Evidence-Based Program (ማስረጃን መሰረት ያደረገ ጥናት)** በጥንቃቄ የተጠና ውጤታማነታቸውን የሚያረጋግጥ ጥናት እና መርሃ ግብር። እነዚህን ያጠቃልላሉ፡- ART, FFT, MST፣ እና FIT።

**Family Court Services (የቤተሰብ የፍርድ ቤት አገልግሎት)** ፍርድ ቤቱ የሚከተሉትን የጉዲፈቻ ፣ የቤተሰብ እቅዶች ፣ የቤትውስጥ አካላቂ ድብደባ እና Becca መህሃግብርን የሚመለከቱ ቢሮዎችን አዘጋጅቷል፡ ARY፣ CHINS እና Truancy።

**Felony (ከባድ ወንጀል)** በተፈጸመ ድርጊት ረዘም ላለ ጊዜ በእስር ቤት ወይም በታዳጊዎች ማረሚያ ቤት እስራትን የሚያስከትል ጠንከር ያለ የወንጀል እርምጃ። JR ን ይመልከቱ (ቀለል ያሉ ወንጀሎች በደል በመባል ይታወቃሉ)

**File charges (የማህደር ክስ)** አቃቢ ህጉ መሰረታዊ የህግ ሂደቱን ተከትሎ ወጣቱን ለመቅጣት የክስ ሂደቱን እንደሚከታተል ይፋዊ የሆነ መግለጫ ነው። ችሎት ይውላል እንዲሁም በልጅዎ የቀረበው ማስራጃ ይቀርባል።

First Appearance Hearing (**የመጀመሪያ የክስ መስማት ሂደት**) ይህ ሂደት ዳኛው ክሱን በቀረቡት ማስረጃዎች መሰረት የተከሰሰው ወጣት ላይ ፍርድ ቤቱ ብያኔን የማስተላለፍ ስልጣን እንዳለው ወይም እንደሌለው የሚወስንበት ነው።

Functional Family Therapy (FFT፣ **ተግባራዊ የቤተሰብ ምክር**) በከፍተኛ አደጋ ውስጥ ለሚገኙ እድሜያቸው ከ 11-18. ለሆኑ ልጆች ለመታደግና ጣልቃ ለመግባት የአጭር ጊዜ በቤት ውስጥ የሚካሄድ መርሃግብር

Guardian (**ሞግዚት**) ለልጁ/ልጅቷ የሚጠነቀቅ እና ምርጫዎችን ለመወሰን ህጋዊ መብት ያለው አዋቂ ሰው። የሞግዚት ስልጣን ለልጁ/ልጅቷ ወላጆች፣ የቤተሰብ አባል፣ ያልተዛመደ አዋቂ ወይም መንግስት ሊሆን ይችላሉ።

Grievance (**ይግባኝ**) ትክክል ባልሆነ ወይም ኢ-ፍትሃዊ በዎነ አያያዝ ላይ ይፋዊ የሆነ ቅሬታ የሚገለጽበት መግለጫ።

Hearing (**የክስ መሰማት**) በፍርድ ቤት ውሳኔ ሰጪ አካል ፊት ከጠበቃ ጋር ወይም በመጠበቂያ ክፈል የሚካሄድ ክስተት።

Jurisdiction (**የፍርድ ስልጣን**) ፍርድ ቤቱ የልጁን/ልጅቷን የህግ ጉዳይ ለማየት ያለው የዳኝነት ስልጣን።

Juvenile (**ታዳጊዎች**) ከአስራ ስምንት አመት እድሜ በታች የሆነ ማንኛውም ግለሰብ።

Juvenile Justice Assessment Team (**የታዳጊዎች የፍትህ ምዘና ቡድን**) ለፍርድ ቤቱ የሚቀርብ ስለታዳጊው ፍርድ ቤቱን መሰረት ያደረገ ምዘና።

Juvenile Detention Officer (**የታዳጊዎች ማረሚያ ቤት መኮንን**) ለታዳጊ ታራሚዎች ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢን የመፍጠር እና የመጠበቅ እንዲሁም የእንክብካቤ እና ፍላጎታቸው መሟላቱን የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለባቸው በእስር ቤት ውስጥ የሚሰሩ ግለሰቦች።

Juvenile Probation Counselor (**የታዳጊዎች አመክሮ አማካሪ ጠበቃ**) ጥፋተኛ መሆኑን ለሚያምን ወይም በፍርድ ቤቱ ጥፋተኛ ሆኖ ለተገኘ ወጣት የተመደበ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ባለሙያ። ከተከሰሸ ታዳጊው እና ከቤተሰቦቻቸው ጋር የጉዳይ እቅድ ያዘጋጃሉ እንዲሁም ለዳኛው ስለ ልጅዎ መረጃን ይሰጣሉ። የአመክሮ አማካሪዎች ዋና ዓላማ ልጅዎን እና ቤተሰብዎን በሂደቱ መደገፍ ነው። እንዲሁም ወደፊት ጠቃሚ የሚሆኑ ሰላማዊ እና ጤናማ ግብዓቶችንም ያቀርባሉ።

Juvenile Rehabilitation (JR፣ **የታዳጊዎች መልሶ ማቋቋም**) በ DCYF የሚገኝ ሲሆን በዋሽንግተን ግዛት የሚገኙን አደጋ ላይ የሚገኙን ታዳጊዎች ያገለግላል። ወጣቶች በማንኛውም የካውንቲው የታዳጊ ወጣቶች ፍርድ ቤት ለ JR ጥበቃ ሊሰጥ ይችላል። የታዳጊዎች ፍርድ ቤት በተቀመጡት የቅጣት መመሪያዎች መሰረት ፍርድን ለታዳጊዎች ያስተላልፋሉ። እነዚህ ወጣቶች በተለምዶ ብዙ ቀለል ያሉ ወንጀሎችን ፈጽመዋል ወይም ከባድ ወንጀል ፈፅመዋል።

Law Enforcement (**ህግ ማስከበር**) የፖሊስ መኮንኖች ሥራቸውን ሕግን ማስከበር ነው። በኪንግ ካውንቲ የመኮንኖች መምሪያ በአካባቢ የሚገኙ ከተሞች እና ማዘጋጃ ቤቶች ጋር የሕግ ማስከበር አገልግሎቶችን ይሰጣል።

Mandated Reporter (**ኃላፊነት የተሰጠው/የተሰጣት ዘጋቢ**) በሙያቸው ምክንያት በሕፃናት ላይ የሚደርሰውን በደል ወይም ቸልተኝነት ማንኛውንም ጥርጣሬ ለህፃናት ጥበቃ አገልግሎት ሪፖርት የማድረግ ግዴታ ያለበት ሰው ነው። የመከላከያ ጠበቆች እና አለዛቢ ስፔሻሊስቶች በግዴታኃላፊነት የተሰጠው/የተሰጣት ዘጋቢ **አይደሉም**።

Mentor (**ጠቋሚ፣መካሪ**) ወጣቶችን በአቅማቸው የሚመራ እና የሚደግፍ ባለሙያ።

Misdemeanor (**አነስተኛ ወንጀል**) ከከባድ ወንጀል በቀለለ እና ያልከበደ ወንጀል

Multi-Systemic Therapy (**ባለብዙ-ሥርዓታዊ ምክር**) እድሜያቸው ከ 12-17 ላሉ ከባድ የባህሪ ችግር ላለባቸው ልጆች ጠለቅ ያለ በቤት ውስጥ የሚካሄድ የምክክር ጊዜ።

**Offense (ጥፋት/ወንጀል)** በአዋቂዎች የተፈጸመ ድርጊት እንደ ጥፋት ወይም ወንጀል ይቆጠራል።

**Parent (ወላጅ)** በዚህ ረገድ "guardian(አሳዳጊ)" እና "parent(ወላጅ)" አንድ አይነት ትርጉም አላቸው።

**Plea Bargain (የእምነት ክህደት ቃል ድርድር)** የተከሳሽ ታዳጊ ጠበቃ እና በዐቃቤ ህግ መካከል የሚደረግ ስምምነት አብዛኛውን ጊዜ ታዳጊው ወንጀሉን በማመን ከቅጣት መጠን ያነሰ ቅጣት ለመጠየቅ የሚስማማበት ነው።

**Probable Cause (አሳማኝ ምክንያት)** ታዳጊው የተከሰሱበትን ወንጀል ለምን እድፈጸሙ አሳማኝ ምክንያት።

**Probation (አመክሮ)** በአመክሮ የተፈቱ ታዳጊ ልጆች በፍርድ ቤቱ((JPC) ክትትል ስር እንዲሆኑ ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው ትዕዛዝ ነው። JPC አስፈላጊ የሆነውን ክትትል እና ምዘናንም ለቤተሰቡ እና ለታዳጊው ያቀርባል።

**Prosecution (የክስ ሒደት)** አንድን በወንጀል የተከሰሰን ግለሰብ ወደ ችሎት የማቅረብ ሂደት።

**Prosecutor (ዓቃቤ ህግ)** የኪንግ ካውንቲ ዓቃቤ ህግ ታዳጊው ላይ ክስን የሚመሰርቱ እና ፍርድን ለማሰጠት የሚሰሩ የህግ ባለሙያ።

**Public Defender (መንግስት የሚያቆመው ጠበቃ)** ጠበቃ መቅጠር ላልቻሉ በኪንግ ካውንቲ ፍርድ ቤት የተሾመ የተከሳሽ ጠበቃ።

**Recidivism (ረሲዲቪዝም)** የተደጋገመ የወንጀል የፍርድ ውሳኔዎች።

**Referral (ሪፈራል)** የህግ አስከባሪው የፖሊስ ሪፖርትን ሲያጣቅስ። በ PC ወይም በአገልግሎት አቅራቢ ስም "ለአገልግሎቶች ሪፈራል" በሚሆንበት ጊዜ እርዳታ ወይም ድጋፍ እንዲያገኙ የሚጠቁም ነው።

**Respondent (መልስ ሰጪ)** በታዳጊዎች ፍርድ ቤት የፌደራልን፣ የግዛትን ወይም የከተማን ህግ በመተላለፍ የተከሰሰው ያዳጊ።

**Restitution (መመለስ)** ለተጠቂ የሚከፈል ክፍያ

**Statute (ደንብ)** በዋሽንግተን ግዛት የህግ አውጪ አካል በስራ ላይ የዋለ ህግ።

**Subpoena (መጥሪያ)** አንድ ሰው በአንድ በተወሰነ ሰዐት እና ቦታ በአካል እንዲገኝ በማዘዝ የሚሰጥ የፍርድ ቤት መጥሪያ።

**Superior Court (ጠቅላይ ፍርድ ቤት)** የታራሚ ታዳጊዎችን አመክሮ፣ የፍርድ ቤት አገልግሎት፣ የቤተሰብ ፍርድ ቤት፣ እና ጸሐፊዎችን፣የአገልግሎት ሰራተኞችን በስልጣን ይመለከታት።

**Testimony(ምስክርነት)** አንድ ሰው በችሎት/ በፍርድ ቤት ፊት የሚሰጠው የእምነት ክህደት የምስክርነት ቃል።

**Truant (ቸልተኛ፣ ታካች)** በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አምስት ወይም በአንድ አመት ውስጥ 10 ጊዜ ሳይፈቀድለት የቀረ።

**Truancy Petition (አውቆ ቀሮችን የማስቆም አቤቱታ)** አውቆ ቀሮችን የማስቆም አቤቱታ የሲቪል አቤቱታ ሲሆን ትምህርት ቤቶች ትማሪዎችን መልሰው ወደ ትምህርት ቤት የመመለስ አቤቱታ ነው።

**Undocumented (ሰነድ-አልባነት)** የአሜሪካ መንግስት ፈቃድ ወይም ምርመራ ሳያስፈልግ በሃገሪቱ ውስጥ ህጋዊ በሆነ ቪዛ ገብቶ አሁን ግን ጊዜው ያለቀ ቢሆንም በህጋዊነት መኖርን ያመለክታል።

**Warrant (ትዕዛዝ)** ፖሊስ አንድን ወጣት ወደ አንድ የተወሰነ ቦታ እንዲይዝ ወይም እንዲያጓጉዝ በሕግ ወይም በመንግሥት ባለሥልጣን የተሰጠ ፈቃድ።

# ምህጻረ-ቃላት

“acronym (ምህጻረ-ቃላት)” ማለት የቃል መነሻ ስብስብ ነው። እነዚህ ብዙውን ጊዜ በሕግ ሥርዓት ውስጥ የሚሰሩ ሰዎች የሚጠቅሟቸው ናቸው። የሚከተሉት በተለምዶ ሰዎች የሚጠቀሟቸው ናቸው።

**ART** Aggression Replacement Therapy (የግልፍተኝነትን የመተካት ቴራፒ)

**ARY** At Risk Youth (አደጋ ላይ ያሉ ታዳጊዎች) በህዝባዊ አቤቱታ የተጀመረ ነው። በ “ትርጓሜዎች” ውስጥ “**<u>በስጋት ላይ ያሉ ወጣቶች</u> አቤቱታ**” ይመልከቱ።

**CABs** Community Accountability Boards (የማህበረሰብ ሃላፊነት ቦርድ)

**CEDAR** Community Empowered Disposition Alternative and Resolution (ማህበረሰብን የማጠናከር ሥርዓት አማራጭ እና መፍትሄ)

**CFJC** Children and Family Justice Center (የህፃናት እና የቤተሰብ ፍትህ ማዕከል)

**CHINS** Child in Need of Services (አገልግሎት የሚያስፈልጋቸው ሕፃናት) አቤቱታ። በ “ትርጓሜዎች” ውስጥ “አገልግሎት የሚያስፈልጋቸው ሕፃናት” ይመልከቱ።

**CPS** Child Protective Services (የልጅ ጥበቃ አገልግሎቶች) በዋሽንግተን ግዛት መምሪያ የህጻናት፣ታዳጊዎች እና ቤተሰቦች

**DAJD** ኪንግ ካዉንቲ Department of Adult and Juvenile Detention (የኪንግ ካውንቲ የአዋቂዎች እና የታዳጊዎች ማረሚያ)

**DCYF** ዋሽንግተን ግዛት Department of Children Youth and Families (የህጻናት፣ታዳጊዎች እና ቤተሰቦች ክፍል)

**DPD** የኪንግ ካውንቲ Department of Public Defense (የሕዝብ መከላከያ ክፍል)

**DSHS** የዋሽንግተን ግዛት Department of Social and Health Services (የማህበራዊ እና የጤና አገልግሎት ቡድን)

**EBP** Evidence Based Program (ማስረጃን መሰረት ያደረገ መርሃግብር)

**FFT** Functional Family Therapy (ተግባራዊ የቤተሰብ ምክር)

**FIRS** Family Intervention and Restorative Services (የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት እና መልሶ ማቋቋሚያ አገልግሎቶች)

**JPC** Juvenile Probation Counselor (የታዳጊዎች አመክሮ ጊዜ አማካሪ)

**JJAT** Juvenile Justice Assessment Team (የታዳጊዎች የፍትህ ምዘና ቡድን)

**JR** Juvenile Rehabilitation (የታዳጊዎች መልሶ ማቋቋም)

**MST** MultiSystemic Therapy (ዘርፈ-ብዙ ምክር)

**PAO** Prosecuting Attorney’s Office (የዓቃቤ ሕግ ቢሮ)

# የማህበረሰብ ሀብቶች እና አገልግሎቶች

የሚከተሉት በኪንግ ካውንቲ ለሚገኙ ታዳጊዎች እና ቤተሰቦች የሚቀርብ አገልግሎት ነው። ለበይነመረብ ቅርብ ከሆኑ ይህንን በመጫን ወይም https://youthresources.kingcounty.gov/ በመሄድ የተሻሻለውን ግብዓት መመልከት ይችላሉ።

4Culture (206) 296-7580
101 Prefontaine Pl S Seattle, WA 98104
ፍርድ ቤቱ የተካተተበት የጥበብ ስራ እና ክህሎቶችን በ16 ሳምንት ትምህርቶች ይሰጣል። በታዳጊዎች የሕግ ሥርዓት ውስጥ ያሉ የዘር ልዩነቶችን ማጥበብ።

Alive and Free (**በህይወት ያለ እና ነጻ**) (206) 749-7550
2100 24th Avenue South, Suite 250, Seattle, WA 98144
በጋንግ ቡድኖች፣ በአመፅ እና በታዳጊዎች ፍትህ ስርዓት ውስጥ ላሉ ታዳጊዎች በማማከር ከአደጋ መከላከል።

Asian Counseling and Referral Services (**ኤዥን የማማከር እና የሪፈራል አገልግሎት**) (206) 695-7600
3639 Martin Luther King Jr. Way S. Seattle, WA 98114
የእስያ ቋንቋዎች አገልግሎት፣ ምዘና፣ ግለሰብ፣ ቡድን፣ እና የቤተሰብ ቴራፒ፣ የጉዳዮች አስተዳደር፣ የቀውስ መልስ፣ የአይምሮ ህክምና አገልግሎት እንዲሁም መድሃኒት። ደቡብ ምሥራቅ እስያ የወጣት ወንዶች ቡድን ፣ አፍላ ዕድሜ ውስጥ የሚገኙ የፍቅር ጓደኝነት ዓመፅ ፕሮግራም ፣ የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀም መከላከል ፣ ትምህርት ፣ የትምህርት ማስኬጃ የገንዘብ ድጋፍ ፣ ሥራ ፣ ማስጠናት ፣ የማህበረሰብ አገልግሎት እና የመዝናኛ ገቢር።

Center for Human Services (**የሰዎች አገልግሎት ማዕከል**) (206) 362-7282
Shoreline የሚገኙ 2 በታዎች
የምክር አገልግሎት ፣ የስፓኒሽ ቋንቋ የአሳዳጊ ትምህርቶች ፣ የአደንዛዥ ዕፅ ሱሰኝነት አገልግሎቶች እና አልባሳት ፣ የኮምፒተር ተደራሽነት ፣ የፀጉር መቆረጫ ቫውቸር ፣ የጨቅላ ሕፃናት ወላጅ ድጋፎች ። ወላጆች Shoreline ያለውን አገልግሎት ሲጠቀሙ ለልጆቻቸው የህጻናት ማቆያን ያዘጋጃል።

Centro Rendú (253) 499-4245
St. Vincent DePaul, Kent, Burien, and Renton
ለላቲን ቋንቋ ተናጋሪዎች የሚሰጥ አገልግሎት። ቀደምት የወላጅነት ክህሎቶች ፣ የመሠረታዊ ትምህርት ክፍሎች ፣ ጂ.ኢ.ዲ. ፣ የኮምፒተር እና የገንዘብ ነክ ትምህርት፣ የጉዳይ አስተዳደር፣ የወጣት እና የጉዳዮች አስተዳደር ፣ ሁከት ፣ እና የአደንዛዥ ዕፅ መከላከል እና የጣልቃገብነት አገልግሎቶች ከትምህርት ቤቶች እና ከአጋር ድርጅቶች ጋር ይሰራል። የኢሚግሬሽን አገልግሎቶች

Changes Parent Support Network (**የቤተሰብ እርዳታ ኔትወርክ ለውጥ**) (888) 468-2620
Discovery House, 4401 2nd Ave NE, Seattle
በተቃዋሚ እና እራስን በሚያጠፉ ባህሪዎች ውስጥ ከሚሳተፉ ልጆች ጋር ለሚታገሉ ወላጆች ድጋፍ የሚሰጥ የተዋቀረ ፣ በእኩዮች የሚመራ ፕሮግራም። Changes ተስፋን፣ እርዳታን፣ እገዛን እና እፎይታን ከመጠን በላይ ለተጨነቀና ብቸኛ ለሆነ ማቅረብ። የሲያትል ስብሰባ ረቡዕ ከቀኑ 7:00-9:30 p.m ይካሄዳል። በየወሩ የመጀመሪያ ረቡዕ ከቀኑ 6:00 p.m ሰዓት ላይ እድለኝነት አላቸው።

Children's Crisis Outreach Response System (CCORS**፣ የልጆች ቀውስ መድረሻ የመልስ ሲስተም**) 206-461-3222
ግጭት በሚገጥማቸው ቤተሰቦች ፣ በስሜታዊነት ወይም በባህሪያቸው ችግር እየገጠማቸው ያሉ ወጣቶች እና ወጣቱ ከመኖሪያ አደረጃጀታቸው የመወገድ ስጋት በሚሆንበት ጊዜ የችግር አገልግሎቶች።

Choose 180 (206) 457-8940
1416 SW 151st ST Burien 98166
አማካሪነትን ፣ ተሟጋችነትን ፣ የሥራ ዕድሎችን ፣ የክረምት ልምዶችን እና የትምህርት ድጋፍን ይሰጣል።

Commercially and Sexually Exploited Children (በንግድ እና በወሲብ ብዝበዛ የተጎሳቆሉ ህጻናት) (206) 205-9534 Office or (206) 601-5563 Cell
የንግድ ወሲባዊ ብዝበዛን ያጋጠማቸው ወይም ለአደጋ የተጋለጡ ሕፃናት እና ወጣቶች እና ለእነዚህ ልጆች እንክብካቤ ለሚሰጡት ግለሰቦች እና ቤተሰቦች የሚሰጡ አገልግሎቶች።

Community Passageways (የማህበረሰብ መተላለፊያ)
7728 Rainier Ave S, Seattle, WA 98118
ለአካለ መጠን ያልደረሰ የሕግ ሥርዓት ውስጥ ለተሳተፉ ወጣቶች እና ወላጆች መማክርት ፣ ተሟጋችነት ፣ የሕይወት ክህሎቶች ፣ በዘር ላይ የተመሠረተ ፈውስ ፣ የፖሊሲ ጥብቅና እና መጓጓዣ ይሰጣል።

Community Psychiatric Clinic (የማህበረሰብ የአይምሮ ክሊኒክ) (206) 366-3015
የተለያዩ ዋና ቦታዎች፦ 4319 Stone Way N Seattle, WA 98103
ዙሪያውን ፣ የተመላላሽ ሕክምና አማካሪ ግምገማዎች ፣ የግለሰብ መማክርት ፣ የወላጅ ድጋፍ ፣ የቤተሰብ ሕክምና ፣ የክህሎት ግንባታ ቡድኖች እና የጉዳይ አስተዳደር አገልግሎቶች።

Consejo Counseling & Referral Services (ኮንሴጆ አማካሪ እና ሪፈራል አገልግሎት) (206) 461-4880
የተለያዩ ዋና ቦታዎች፦ 3808 S Angeline Street Seattle, WA 98118
ለላቲንክስ ፣ ለአደጋ ተጋላጭ ወጣቶች እና ለቤተሰቦቻቸው እንደ ጋንግ ፣ ዓመፅ ፣ እና የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀም መከላከል እና ጣልቃ ገብነት ፣ ማስተማሪያ ፣ መምሪያ ፣ የመዝናኛ እንቅስቃሴዎች ፣ የአካዳሚክ ትምህርቶች ፣ የተመላላሽ ህመምተኞች የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች ፣ በትምህርት ቤት ላይ የተመሠረተ የምክር ፕሮግራም ፣ ወሲባዊ ጥቃት መከላከል ፣ ምስላዊ እና አፈፃፀም ስነ-ጥበባት እና የማህበረሰብ አገልግሎቶች።

Credible Messengers (ታማኝ መልእክተኞች) (206) 981-1190 (253) 335-6731 & (206) 261-2410
ከወጣቶች ጋር በዘር፣ በባህል፣ በማህበራዊ እና በምጣኔ ሃብት እንዲሁም በኑሮ የሚመሳሰሉ መካሪዎች። የሕይወት ችሎታ ፣ ተሟጋችነት ፣ ስኬት ፣ በዘር ላይ የተመሠረተ ፈውስ ፣ ኃይል መስጠት እና አካዴሚያዊ እቅድ።

Crime Victims Compensation (CVC፣የወንጀል ሰለባዎች ካሳ) (800) 762-3716
የህክምና፣ ምክር እና የተወሰነ የጠፋን ክፍያ ለንጹህ የወንጀል ሰለባዎች ይከፍላል።

Employment and Education Youth Services (የታዳጊዎች ስራ ቅጥር እና የትምህርት አገልግሎት) (206) 477-7000
WorkSource Center 645 Andover Park West Tukwila, WA 98188

Friends of Youth (የታዳጊ ጓደኞች) (425) 869-6490
ኢሳኩዋ
የመካከለኛ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ዙሪያ መጠበቂያ አገልግሎቶች ፣ የተመላላሽ ታካሚ አማካሪ እና የቤት እጦት መከላከል የሕይወት ክህሎቶች ሥልጠና እና የወጣት መጠለያዎች።

Glover Empowerment Mentoring (GEM፣ ግሎቨር ማብቃት እና ማማከር) (253) 277-2726
827 N Central Ave Suite B-109 Kent, WA 98032
የግለሰብ፣ የቡድን እና የትምህርት ቤትን መሰረት ያደረገ ምክር።የጉዳይ አስተዳደር ፣ ተሟጋችነት ፣ የችግር ድጋፍ ፣ የጎዳና ላይ ተደራሽነት እና የስርዓት አሰሳ።

Greater Maple Valley Community Center (ግሬተር ሜፕል ቫሊ የማህበረሰብ መዐከል) (425) 432-1272
የመታቀብ እና የማማለድ የታዳጊ ልጆች መርሃ ግብር። ከ 6 ኛ እስከ 12 ኛ ክፍል ላሉት ወጣቶች ፕሮግራሞች ፣ የእኩዮች እንቅስቃሴዎች ፣ በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ የሚገኙ የፍቅር ጓደኝነት ዓመፅን መከላከል ፣ የበጋ ፕሮግራሞች ፣ ትምህርት ፣ የምክር አገልግሎቶች እና የ LGBTQ አገልግሎቶች።

Guided Pathways Support for Youth and Families (የተጋረደ መንገድ እርዳታ ለወጣቶች እና ቤተሰቦች) (253) 236-8264
የታዳጊዎች እና ቤተሰቦች የእርዳታ መስመር ማክሰኞ እና ሃሙስ 9:00 AM - 5:00 PM (253) 277-4052
6625 S. 190th St., Suite B108, Kent, WA 98032

በእንክብካቤ ስርዓት ውስጥ ለተሳተፉ የልጀ ወላጆች 1-1 ድጋፍ ይሰጣል። የወላጆች ትምህርት እና ስልጠና ለወላጆች እገዛ ማቅረብ። ለታዳጊዎሽ የጓደኛ እርዳታ። የቤተሰብ ማህበራዊ ክስተቶች

[Harborview Medical Center Traumatic Stress Counseling (**ሃርበርቪው የህክምና ማዕከል ለስሜት ቀውስ ጭንቀት ማማከር**)] (206) 744-1600 ሲያትል
(425) 688-5130 Bellevue
ለሁሉም አይነት የወንጀል ሰለባ ለሆኑ የምክር አገልግሎት ማቅረብ።

[Helping Youth Perform Excellence HYPE (**ታዳጊዎችን በልቀት ብቁ እንዲሆኑ ማድረግ**)] (253) 740-8198
ፌደራል ዌይ
እድሜያቸው ከ14-18 የሚሆኑ እና ለአመክሮ የተዳረጉ ታዳጊዎችን በሁለት ሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ መርሃ ግብር ላይ ማካተት። በማህበረሰም መሪዎች የሚካሄድ የአመራር እና የህይወት ተሞክሮ ትምህርት። የስኬት እቅድ እና እርዳታ።

[Horn of Africa (**የአፍሪካ ቀንድ**)] (206) 760-0550
5303 Rainier Ave. S. Suite D Seattle, WA 98118
የጉዳዮች አስተዳደር እና የስራ ዝግጅት በአማርኛ፣ ኦሮሚኛ፣ ትግርኛ እና ሶማሊኛ። በኪንግ ካውንቲ የሚገኙ የምስራቅ አፍሪካ ስደተኞችን ያገለግላል።

[The IF Project]
ማብራሪያ

[Journeymen] (206) 429-5203
Vashon Island
በተፈጥሮ ላይ በተመረኮዙ ቀጣይነት ባላቸው የምክር አገልግሎቶች ለወንዶች ልምምዶችን ማዳበር። ካምፖች፣ ወርክሾፖች፣ መዝናኛዎሽ፣ ወዘተ

[Kent Youth and Family Services (**ኬንት የታዳጊዎች እና የቤተሰብ አገልግሎት**)] (253) 859-0300
232 2nd Ave. S. Ste 201 Kent, WA 98032
የአእምሮ ጤንነት እና የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀም ጣልቃ ገብነት አገልግሎቶች ፣ LGBTQ (ኤልጂቢቲኪው) እና አጋሮች ድጋፍ ቡድን ከ 13 እስከ 19 ዕድሜ ላላቸው ወጣቶች ፣ የታዳጊዎች መድረስ፣ ከትምህርት ቤት በውሃላ መርሃግብሮች እንዲሁም የጎዳና ትዳዳሪነትን መታደግ ይካተታሉ።

[King County Sexual Assault Resource Center (KCSARC፣ **ኪንግ ካዉንቲ የወሲብ ጥቃት መዝገብ ማእከል**)] (425) 226-5062
የ 24-ሰዓት የቀውስ መልስ መስመር (888) 998-6423
200 Mill Avenue South, Suite 10 Renton, WA 98057
ምክርን፣ ሙገታን፣ የህግ ትሟጋችነትን፣ የቤተሰብ እርዳታን፣ እና የቀውስ ጊዜ አገልግሎትን የወሲብ ጥቃትን ላሳለፉ ሰዎች ያቀርባል። በስፓኒሽ ቋንቋም እርዳታን ያቀርባሉ።

[King County Wraparound WISE] (206) 263-8957 or (206) 263-9006
የወጣት ታዳጊዎችን ውጤት ለማሻሻል በቡድን ላይ የተመሰረተ የእቅድ አወጣጥን በመከተል ውስብስብ ፍላጎቶችን እና ቤተሰቦቻቸውን ማገዝ።

### የትምህርት ማዕከላት
Shoreline Community College (206) 533-6733
Seattle Vocational Institute (206) 934-4439

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ያላጠናቀቁ ነገር ግን GED ን ማግኘት እና ወደ ኮሌጅ ፣ ቴክኒካዊ ሥልጠና እና / ወይም ሥራ ለመቀጠል የሚፈልጉ ከ 16 እስከ 24 ዓመት ዕድሜ ውስጥ ያሉትን ወጣቶች ያገለግላል። የትምህርት ተሟጋችነት እና ጉዳይ ማስተዳደር።

[Mentoring Urban Students and Teens (M.U.S.T.፣ **የከተማ ተማሪዎችን እና ታዳጊዎችን ማሰልጠን**)](#) (206) 949-7444
4093 Letitia Ave S. Seattle, WA 98118
ደመወዝ የሚከፈላቸው የኮሌጅ ተማሪዎች ከ 8 ኛ ክፍል ጀምሮ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ድረስ ያሉ ወጣቶችን በሬየር ሸለቆ ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች ጋር ይመካከራሉ።

[Mercer Island Youth and Family Services (**መርሰር ሲሴት የታዳጊዎች እና የቤተሰብ አገልግሎት**)](#)
በትምህርት ቤት ላይ የተመሠረተ የምክር አገልግሎት እና የተመላላሽ ታካሚ የቤተሰብ ሕክምና።

[National Suicide Prevention Lifeline (**ብሔራዊ ራስን የማጥፋት መከላከያ የሕይወት መስመር**)](#) (800) 273-8255 TTY (800) 799-4889
ሕይወት መስመር 24/7 ነፃ እና ምስጢራዊ ድጋፍ በችግር ውስጥ ላሉት ሰዎች ፣ መከላከያ እና ቀውስ ሀብቶች ለእርስዎ ወይም ለሚወዷቸው ሰዎች ይሰጣል።

[Navos](#) (206) 248-8826
የተለያዩ ቦታዎች ዋና፡ 2600 SW Holden Street, Seattle, WA 98126
በሽተኛ እና የተመላላሽ ክሊኒክ ፣ ቤት እና ትምህርት ቤት የተመሰረቱ የወጣቶች የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች።

[Neighborhood House (**የመንደር ቤቶች**)](#) (206) 461-8430
ሲያትል እና ኦበርን የሚገኙ ቦታዎች
ከትምህርት በኋላ ፕሮግራሞች ፣ ለከፍተኛ ነጥብ ነዋሪዎች የቤተሰብ መገልገያ ማዕከል እና ለወጣቶች የትምህርት እና የቅጥር አገልግሎቶች።

[North Shore Youth and Family Services (**ኖርዝ ሾር የወጣቶች እና ቤተሰብ አገልግሎት**)](#) (425) 485-6541
19201 120th Ave. NE Ste 108 Bothell, WA 98011
የአእምሮ ጤንነት ፣ የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀም ምክር ፣ የወላጅነት ትምህርቶች እና በትምህርት ቤት ድጋፍ ፕሮግራሞች ውስጥ።

[Open Doors for Multicultural Families (**ለብዝሃ-ባህል ቤተሰቦች ክፍት በሮች**)](#) (253) 216-4479
24437 Russell Rd., Suite # 110 Kent, WA 98032
ለወጣቶች፣ ለወጣቶቹ ቤተሰቦች እና የተለያዩ ቋንቋዎችን ለሚናገሩ የአካል ጉዳተኛ ልጆች ድጋፍ ይሰጣል። ለወጣቶች እና ለወላጆች በባህላዊ ምላሽ የሚሰጡ የችሎታ ልማት አውደ ጥናቶች ፣ የድጋፍ ቡድኖች ፣ የሥራ ዝግጁነት እና የሕይወት ችሎታዎች ፣ የቤት እጦትን መከላከል ፣ ተሟጋችነት ፣ የሥርዓት አሰሳ ፣ የመዝናኛ እንቅስቃሴዎች ፣ ወዘተን ያካትታል።

[Parent for Parent (**ወላጅ ለወላጅ**)](#) (206) 477-2311
[Superior Court, Seattle and Maleng Regional Justice Center, Kent (**ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ ሲያትል እና ማሌንግ ክልላዊ የፍትህ ማዕከል፣ ኬንት**)](#)
የበላይ ፍርድ ቤት ልጆቻቸው በልጆች ጥበቃ አገልግሎት (CPS) የተያዙ ወይም ልጆቻቸው በቤት ውስጥ ጥገኛ ውስጥ ያሉ ወላጆቻቸውን ለመርዳት ፕሮግራም ያቀርባል ። "Parent Allies (የወላጅ ትብብር)" ለስርዓቱ አዲስ የሆኑን ወላጆች ከሌሎች ስርዓቱን ከሚያውቁ ጋር ማገናኘት። የወላጅ አጋሮች ከልጆቻቸው ጋር እንደገና ለመገናኘት ምን ማድረግ እንዳለባቸው እንዲገነዘቡ Parent Allies ለሥርዓቱ አዲስ ለሆኑ ወላጆች ይረዳል።

መርሃግብሩ ሰስት ዋና ዋና ነገሮችን የያዘ ነው፡-Parent Ally(የቤተሰብ አጋር) በጥግኛ የፍርድ ቤት ችሎት ላይ የሁለት ሰዓት Dependency 101 (ጥገኝነት 101) የተሰኘ፣ እና በሂደት ላይ ያለ Dependency 201 (ጥገኝነት 201) የተሰኘ ትምህርትን ይሰጣል።

[Positive Outcomes Program (**አዎንታዊ ውጤት መርሃግብር**)](#) (253) 838-6810
ፌደራል ዌይ
የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ምረቃ ወይም GED ማግኘትን የሚደግፍ የወጣት ፕሮግራም ፣ በኮሌጅ ወይም በስልጠና ፕሮግራም መመዝገብ ፣ ሥራ ማግኘት ፣ እንደ መጓጓዣ ፣ የትምህርት ቤት ቁሳቁሶች ፣ አልባሳት ፣ መኖሪያ ቤት ወይም ምግብ ያሉ ግብዓቶችን የማግኘት እና በአወንታዊ እንቅስቃሴዎች ይደግፋል።

[Powerful Voices (ሃያል ድምጾች)](#) (206) 860-1026
1620 18th Ave. Ste. 100 Seattle, WA 98122
በትምህርት ቤት እና በክረምት ፕሮግራሞች ፣ የባህል ማበልፀጊያ ፕሮግራሞች ፣ የሥራ መርሃግብሮች እና የሥርዓተ-ፆታ የሁለትዮሽ ላልሆኑ ሴት ተለይተው ለሚታወቁ እና ወጣቶች የጥብቅና ልማት ።

[Puget Sound Adlerian Society](#) (206) 527-2566
ነፃ የ 14 ሰዓት አዎንታዊ የስነምግባር ትምህርት አስተዳደግን እና የኦንላይን የወላጆች ዝግጅት ካላንደር, እንዲሁም ሌሎች ተባባሪዎችን እና የድርጅቶችን የወላጅነት ትምህርት እና የሥልጠና ኮርሶች መረጃ በማዕከላዊ ፓጀት የድምጽ አካባቢዎች ውስጥ ያዘጋጃሉ።

[Reconnect to Opportunity (ከእድሎ ጋር መልሰው ይገናኙ)](#) (206) 263-8244
ዕድሜያቸው ከ 16 እስከ 24 ዓመት ለሆኑ ወጣቶች የትምህርት ትስስር አገልግሎቶችን መልሶ ለማገናኘት የቤትለቤት አገልግሎት መስጠት ። የዘላቂ ስራ እርዳታንም መስጠት።

[Renton Area Youth & Family Services (የሬንትን አካባቢ የታዳጊዎች እና የቤተሰብ አገልግሎት)](#) (425) 271-5600 or (206) 772-2050
1025 South 3rd St. Renton, WA 98057 and 12704 76th Ave. S Seattle, WA 98178
የቤተሰብ መድሃኒት እና የባህሪ ጤና ምክር። የጉዳይ አስተዳደር እና ከአደጋ የመታደግ ስራን በ SPARK T.H.I.S. መርሃግብር

[Ryther](#) (206) 525-5050
2400 NE 95th St. Seattle, WA 98115
በ ‹ADHD› በሽታ ለተያዙ ወጣቶች ሕክምና እና ምክር ለወጣቶች ሕክምና እና ክህሎቶችን ማስተማር። Attention Deficit Hyperactivity Disorder (ADHD፣ አቴንሽን ዴፊሲት ሃይፐርአክቲቪቲ ዲሶርደር)የወጣቶች የእጽ አጠቃቀም ግምገማዎች እና ጣልቃ ገብነቶች ።

[SafeFutures Youth Center (የወደፊት ደህንነት የታዳጊዎች ማዕከል)](#) (206) 938-9606
6337 35th Ave. SW Seattle, WA 98126
በሕግ ሥርዓት ውስጥ የመግባት አደጋ ተጋላጭ ለሆኑ ወጣቶች እና በአሁኑ ወቅት ተሳታፊ ለሆኑ ወጣቶች ባህላዊ ምላሽ ሰጪ የመከላከያ እና ጣልቃ ገብነት መርሃግብሮች። ቢሮዋቸው ሚገኘው ምእራብ ሲያትል ቢሆንም በኪንግ ካውንቲ አገልግሎቶችን ይሰጣሉ። በትምህርት ቤት ተሳትፎ ፣ በመመካከር ፣ በመከራከር ፣ በጉዳዩ አያያዝ እና በሌሎችም የግብዓት ፍላጎቶች ላይ እገዛ ያደርጋሉ።

[SeaMar](#)
የተለያዩ በታዎች
በእንግሊዘኛ እና በስፓኒሽ አገልግሎት መስጠት። የላቲን ትምህርታዊ ስኬት መርሃግብር። የተጠናከረ የጉዳይ አያያዝ ፣ በትምህርት ቤት እንደገና ተሳትፎ ፣ የአደንዛዥ ዕፅ/የአልኮል ምክር ፣ በቤተሰብ ምክር ፣ በጤና አገልግሎቶች እና በወጣቶች የፍትህ ስርዓት ውስጥ ለተሳተፉ ወጣቶች የቤት ድጋፍ ፣ እገዳው ለአደጋ የተጋለጡ የመለስተኛ ደረጃ ተማሪዎች እና በህብረተሰቡ ውስጥ በሚከሰቱ ሁከቶች። ወጣቶችም የሥራ ስምሪት ድጋፍን ፣ የሁለተኛ ደረጃ አሰሳ ዕድሎችን እና የማህበረሰብ አገልግሎት ዕድሎችን ይቀበላሉ።.

[Seattle Children's (የሲያትል ልጆች)](#) (206) 987-2000
4800 Sand Point Way NE Seattle, WA
የወላጅ ክፍሎች እና የድጋፍ ቡድኖች ፣ ለአዋቂዎች የጉርምስና ልማት ሥልጠና ፣ የእኩዮች ምክር ፣ የትምህርት ግብዓቶች። የአካል ጉዳት ተጠቂ ታዳጊ ወልጆችን የሚደግፍ ነው።

[Sound](#) (206) 901-2000
6400 Southcenter Blvd. Tukwila, WA 98188
የታዳጊዎች ጠቅላላ አገልግሎቶች። የተመላላሽ ታካሚ ፣ ማህበረሰብ እና በትምህርት ቤት ላይ የተመሰረቱ አገልግሎቶች። የወጣት እና የቤተሰብ ግለሰብ ፣ ቡድን እና የቤተሰብ የምክር አገልግሎት። ግምገማዎች ፣ የጉዳይ አያያዝ ፣ የችግር ምላሽ ፣

የአእምሮ ሕክምና አገልግሎቶች እና የሥራና የቤት ድጋፍ። የቤተሰብ ወዳጆች እና የጓደኛ አማካሪዎች። የስሜት ቀውስ ይሚሰቃዩ ሰዎችን እና የኦቲዝም ተጠቂ ህጻናት የሚሆን ልዩ አገልግሎት መስጠት።

**Southeast Youth & Family Services (የደቡብ ምስራቅ የወጣቶች እና ቤተሰብ አገልግሎት)** (206) 721-5542
3722 ሳውዝ ሀድሰን መንገድ ሲያትል፣ ዋሽ 98118
ማማከር፣ የልጆች እድገት፣ እና የወጣቶች ልማት መርሃግብሮች። ማህበራዊ እና ህይወት የሚገነቡ ትምህርቶች፣ ባህላዊ እና መዝናኛ ገቢር እና ትምህርታዊ እርዳታ እንደ የጉዳይ አያያዝ እና የምክር አገልግሎት ያሉ የቤተሰብ እና የወላጅ ድጋፍ። የአፍሪካ ስደተኞች እና የስደተኞች አገልግሎት መርሃግብር (የጉዳይ አስተዳደር ፣ የሥራ ድጋፍ እና የባህል ማስተካከያ እና ዝንባሌ) የእስያ ስደተኞች ድጋፍ እና የውጭ ግንኙነት መርሃ ግብር የምክር ፣ የጥብቅና ፣ የመረጃ እና ሪፈራል እንዲሁም የቀውስ ጣልቃ ገብነት እንዲሁም የጉዳይ አያያዝ ፣ የቅጥር ድጋፍ እና የባህል ማስተካከያ እና አቅጣጫን ይሰጣል። የትርጉም አገልግሎቶችም ይቀርባሉ።

**Southeast Youth & Family Services (የደቡብ ምዕራብ የወጣቶች እና ቤተሰብ አገልግሎት)** (206) 937-7680
4555 ደልሪጅ ዌይ ደቡብ ምእራብ ሲያትል፣ ዋሽ 98106
የወጣት እና የቤተሰብ ግለሰብ ፣ ቡድን እና የቤተሰብ የምክር አገልግሎት። አዲስ ወደፊቶች ፣ አርቲስት ፣ የወጣቶች ሁከት መከላከል ፕሮግራም ፣ መጠቅለያ አገልግሎቶች ፣ የጥብቅና እና የጉዳይ አያያዝን ፣ ከትምህርት ውጭ መርሃ ግብሮች ፣ የክረምት ፕሮግራሞች እና የመዝናኛ እንቅስቃሴዎችን ይሰጣል ።

**Substance Abuse Hotline(የሱሰኝነት ፀባይ ምክር ሆትላይን)** (800) 662-4357
የአእምሮ እና / ወይም የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀም ችግር ላለባቸው ግለሰቦች እና ቤተሰቦች 24/7 ፣ 365-በዓመት የሕክምና ማስተላለፍ እና የመረጃ አገልግሎት (በእንግሊዝኛ እና በስፔን)

**Suicide Crisis Text Line (ራስን የማጥፋት ቀውስ የመእክት መስመር)**
በ741741 ላይ START ብለው በመላክ በየትኛውም ቦታ ቢሆኑ ለ 24 ሰዓት እርዳታን ሊያገኙ ይችላሉ። መልክት ላኪው Crisis Counselor(የችግር ጊዜ አማካሪ) በችግር ጊዜ ውስጥ ስላለ ወደ ተረጋጋ ሁኔታ ለማምጣት የሰለጠነ ፣ ከችግር ጊዜ አማካሪ ጋር በቀጥታ የሚከናኝ ነው። ይህንንም በንግግር፣ በማዳመጥ እና በትብብር መፍትሄን ያመጣል።.

**TeamChild** (206) 322-2444
1225 ደቡብ ዌለር መንገድ 420 ሲያትል፣ ዋሽ 98144
ድብቅ መዝገብ ያላቸው ክሊኒኮች። እንደ ትምህርት ነክ፣ መኖሪያ ቤት ፣ የአሳዳጊ እንክብካቤ ፣ ያልተሟሉ የጤና አጠባበቅ ፍላጎቶች ፣ የህግ ስርዓት ላይ እገዛ ለሚፈልጉ ማንኛውም የሕግ ሙገታ።

**Teen Clinics by Seattle and King County Public Health (የታዳጊዎች ክሊኒክ በሲያትል እና ኪንግ ካውንቲ ማህበራዊ ጤና)**
ኦበርን፣ ኢስትቤይ፣ ፌደራል ዌይ፣ ኬንት
ከ21 አመት በታች ለሆኑ ነጻ እና አነስተኛ ወጪ ያለው አገልግሎት ይሰጣል። ነጻ ኮንዶሞች፣ የወሊድ መቆጣጠሪያ፣ የአባላዘር እና የኤች አይ ቪ ምርመራ፣ ፕላን ቢ(ሞርኒንግ አፍተር ፒል)፣ የእርግዝና ምርመራ እና ስለ ወሲባዊ ጤና ያማክራል።

**Teen Link** (866) 833-6546
ስም-አልባ የስልክ እርዳታ ለታዳጊዎች። ምሽት 6:00pm- 10:00pm.

**TXT 4 HELP** 44357
አገር አቀፍ ለ24-ሰዓት የሚያገልግሉ መልዕክት-ላኩ-እገዛ-ከፈለጉ መጠቀም ይችላሉ። ለጉዳት ፣ ለጉልበተኝነት ፣ ለቤተሰብ ችግሮች ፣ ለድብርት ፣ ራስን የማጥፋት ሀሳቦች እና ሌሎችም ምክንያት ድጋፍ ወይም ደህንነት ለመፈለግ ሊያገለግል ይችላል። TXT 4 HELP አማካሪዎች በቴክስት እርዳታን ማቅረብ ይችላሉ። እንዲሁም የተሻለ አማራጮችን መጠቆም ይችላሉ። የሚከተለውን ቃል በፅሁፍ ይላኩ "safe" and እንዲሁም ያሉበትን ቦታ (አድራሻ፣ ከተማ፣ ግዛት) በሚከተለው የቃል ጽሁፍ ላይ ይላኩ 4HELP (44357). በጥቂት ሴኮንዶች ውስጥ በአቅራቢያዎ ያለን Safe Place (አደጋን የማያስከትል እና የሚያስተማምን

በታ) አድራሻ እና በአካባቢው የሚገኙን የታዳጊዎች ኤጀንሲ ስልክ ቁጥር በመልእክት ይደርሶታል። አስቸኳይ እርዳታን ከፈለጉ፣ የሚከተለውን ፅሁፍ ይላኩ "2chat" ከዚያም ከስልጡን አማካሪ ጋር መገናኘት ይችላሉ።

**Therapeutic Health Services (THS)(ቴራፒዩቲክ የጤና አገልግሎቶች)** (206) 323-0930
የተለያዩ በታዎች
የከባቢያዊ አገልግሎቶች ፣ የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀም እና የአእምሮ ጤና ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች ፣ የ 5 ሳምንት የስፓኒሽ የወላጅ አሰልጣኝ ቡድን በጋራ ለሚከሰቱ ውስብስብ ችግሮች። በትምህርት ቤት ላይ የተመሰረቱ አገልግሎቶች በማድሮና መካከለኛ ትምህርት ቤት እና በጋርፊልድ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እንደ የቦታ ግምገማ ፣ የችግር ጣልቃ ገብነት ፣ የግለሰብ እና የቡድን ምክር ፣ የኃይል እና የቡድን ጣልቃ ገብነት / መከላከል ፣ የሀብት ግንኙነት እና ለአፍሪካ የዘር ግንድ ወጣቶች የሕይወት ክህሎቶች ክፍል።

**Urban Artworks(የከተማ የጥበብ-ስራዎች)**
Inscape Arts Building 815 Seattle Blvd S Ste B7 Seattle, WA 98134
ከትምህርት ቤት እና ከውስጥ ሚውራል ሥልጠና መርሃግብር በኋላ ፣ የቅጥር መርሃግብር፣ የክረምት መርሃግብር፣ ሞግዚት ፣ የሥልጠና መርሃግብር። EET በአመክሮ ከእስር ለትለቀቁ ወጣቶች የመርሃግብሩ ተባባሪ።

**Urban Impact(የከተማ ተጽዕኖ)** (206) 722-2052
7728 Rainier Ave. S Seattle, WA 98118
ከትምህርት ቤት ድጋፍ በኋላ ፣ ከአባት ተሳትፎ እና ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በኋላ ለስደተኞች ተማሪዎች ማስተማሪያ የሚሰጡ ፣ ከማዕከላዊ ወረዳ እስከ White Center የተለያዩ ማዕከላት ።

**Urban League of Metropolitan Seattle (የሜትሮፖሊታን ሲያትል የከተማ ሊግ)** (206) 461-3792
105 14th Ave. Ste 200 Seattle, WA 98122
ትምህርት ፣ መኖሪያ ቤት እና የሥራ ስምሪት ድጋፍ ፣ የወጣቶችን የማጎልበት ፕሮግራሞች እና ለወጣት ባለሙያዎች የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች።

**Valley Cities Counseling and Consultation (የሸለቆ ከተሞች አማካሪ እና የምክር አገልግሎት)** (253) 833-7444
የተለያዩ በታዎች

**Vashon Youth and Family Services (ቫሽን የወጣቶች እና ቤተሰብ አገልግሎት)** (206) 463-5511
20110 Vashon HWY SW Vashon, WA 98070
የጉዳይ አያያዝ ፣ የምክር አገልግሎት ፣ የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀም አገልግሎቶች ፣ የንብረት ድጋፍ ፣ የምግብ ጓዳ ፣ የጥርስ አገልግሎቶች ፣ ተሟጋችነት ፣ የቤት እጦት መከላከል ፣ የተደገፈ አኗኗር ፣ ለነፍሰ ጡር ሰዎች የሚደረግ አገልግሎት ፣ የወላጅነት አገልግሎት ፣ የላቲንክስ አገልግሎት አሰጣጥ አገልግሎቶች እና የኃይል መከላከል አገልግሎቶች።

**Victim Support Services (የተጠቂዎች እርዳታ አገልግሎት)** (800) 346-7555 (24-Hour helpline)
ቀደም ብለው እንደሚታወቁት Families & Friends of Violent Crime Victims (የጠበኛ ወንጀል ፈጻሚዎች ቤተሰብ እና ጓደኞች)ለሁሉም አይነት የወንጀል ሰለባ ለሆኑ የምክር አገልግሎት ማቅረብ።

**Washington Recovery Help Line (ዋሽንግተን የማገገሚያ እርዳታ መስመር)** (866) 789-1511
ለአደንዛዥ ዕፅ ሱሰኞች ፣ ለችግር ቁማርተኝነት እና ለአእምሮ ጤንነት የ 24 ሰዓት ስሜታዊ ድጋፍ እና ጥቆማዎች።

**YMCA(ወወክማ)**
የተለያዩ በታዎች
ለወጣቶች እና ለአዋቂዎች የሚሰጡት አገልግሎቶች መኖሪያ ቤት እና የሽግግር ዕቅድ ፣ ትምህርት እና ሥራ ፣ የቤተሰብ ድጋፍ እና አሳዳጊ እንክብካቤ ፣ የምክር እና ቴራፒ ፣ የአመራር ልማት እና ዓመፅ መከላከልን ያካትታሉ።

**You Grow Girl (አንቺ ሴት ልጅ እደጊ)** (206) 417-9904
2200 Rainier Ave S, Suite 201, Seattle, WA 98144

የቀን ካምፖች ፣ የክህሎት ግንባታ ቡድኖች ፣ የሙያ ማማከር ፣ የጉዳይ አስተዳደር ፣ የግለሰብ እና የቤተሰብ ምክር ፣ የስነ-ልቦና ትምህርት እና ከ 7 እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሕፃናት እና ወጣቶች ድጋፍ ሰጪ ቡድኖች።

[Young Women Empowered (Y We)(**የወጣት ሴቶችን ማብቃት፣ማጠናከር**)](#) (206) 519-2426
2524 16th Avenue S. Suite #301 Seattle, WA 98144
Y-WEየአማካሪነት እና የማጎልበት መርሃግብሮች ዕድሜያቸው ከ 13-24 ዓመት ለሆኑ የተለያዩ ወጣት ሴቶችን እና በትልቁ የሲያትል አከባቢ ያሉ የጎልማሳ ሴቶች በማማከር ያገለግላሉ። Y-We በተለምዶ አግባብነት ባላቸው መርሃግብሮች አማካይነት በአሳዳጊዎች የተደገፈ ትርጉም ያለው ተሳትፎ።

[YouthCare](#) (800) 495-7802
ለታዳጊዎሽ የመጠለያን መርሃግብር ፣ የታዳጊዎች ፍርድ ስርዓትን ማገዝ ፣ የቤት እጦትን መከላከል ፣ ለአስተማሪነት እና ለወሲባዊ ጥቃት እና ለንግድ እና ለወሲባዊ ብዝበዛዎች የከለላን መርሃግብሮችን ይሰጣል ።

[Youth Eastside Services (YES፣ **የወጣቶች ምስራቃዊ አገልግሎቶች**)](#) (425) 747-4937
Bellevue, Kirkland, and Redmond
በማስረጃ ላይ የተመሠረተ የአእምሮ ጤና ምክር ፣ የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀም ፣ ተያያዥነት ያለው ምክር እና ሕክምና ፣ የአእምሮ ሕክምና አገልግሎቶች ፣ እና በቀላሉ በኪንግ ካውንቲ ውስጥ ለልጆች ፣ ለወጣቶች እና ለቤተሰቦቻቸው የትምህርት እና የመከላከያ መርሃ ግብር ። በስፓኒሽ ቋንቋም አገልግሎት ያቀርባሉ።

[Youth and Family Clothing Shop at Juvenile Court (**በታዳጊዎች ፍርድ ቤት የወጣቶችና የቤተሰብ የልብስ ሱቅ**)](#) (425) 531-1756
1211 E. Alder St. Seattle, WA 98122
ለተቸገሩ ወጣቶች እና ከወጣቶች የፍትህ ስርዓት ጋር ለሚሳተፉ ቤተሰቦች የልብስ ባንክን ማዘጋጀት ።

[YouthSource](#) (206) 477-7010
የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ለለቀቁ ከ 16-24 ዕድሜ ላላቸው ወጣት ታዳጊዎሽ በርካታ መርሃግብሮችን የሚያቀርብ የአንድ-ማቆሚያ ማዕከል ። እነዚይ መርሃግብሮች በትምህርት፣ በስራቅጥር እና በአመራር ልማት ላይ ያተኩራሉ። እንዲሁም ከወጣቶች ፕሮግራሞች ፣ ለህይወት ማረጋጋት የማህበረሰብ ሀብቶች ፣ ለሥራ ዝግጁነት እና ምደባ አገልግሎቶች ፣ እና ሁሉን አቀፍ የጉዳይ አስተዳደር ግንኙነቶችን ይሰጣሉ።

# እውቅናዎች

**Content adapted from** the "King County Juvenile Justice Resource Booklet(የኪንግ ካውንቲ የግብዓት ቡክሌት)" developed by Juvenile Justice 101(የታዳጊዎች ፍትህ), "A Family Guide to Pennsylvania's Juvenile Justice System Developed by the Family Involvement Committee of the Pennsylvania Council of Chief Juvenile Probation Officers(ለፔንሲልቬንያ የሕፃናት ፍትሕ ስርዓት የቤተሰብ መመሪያ በፔንሲልቬንያ ዋና የሕፃናት የሙከራ ባለሥልጣናት ምክር ቤት የቤተሰብ ተሳትፎ ኮሚቴ)" and the Parents of Incarcerated Children Bill of Rights(የታሰሩ ህጻናት ወላጆች መብት) ከ Texas Juvenile Justice Division(ቴክሳስ የታዳጊዎች የፍትህ መምሪያ).

**Zero Youth Detention (ZYD፣ ዜሮ የወጣቶች እስር) የሚከተሉን ስለማይነገር ሰዓታቸው፣ ለሰጡን አስተያየት፣ ሃሳብ እና ምክር ያመሰግናል።** የኪንግ ካውንቲ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የታዳጊዎች ፍ/ቤት አገልግሎቶች፣ የኪንግ ካውንቲ የሕዝብ መከላከያ መምሪያ፣ የኪንግ ካውንቲ ዓቃቤ ሕግ ቢሮ፣ የአፈፃፀም፣ የስልት እና የበጀት ቢሮ፣ ኪንግ ካዉንቲ እና ሲያትል የህዝብ ጤና፣ የኪንግ ካውንቲ የአዋቂዎች እና የታዳጊዎች ማቆያ መምሪያ፣ ለልጆች ጥሩ ጅማሬዎች፣ የኪንግ ካውንቲ የባህሪ ጤና እና ማገገሚያ ዲቪዥን፣ የኪንግ ካውንቲ የቤተሰብ እና የወጣት ካውንስል፣ Anita Asphy, Shalynn Coleman, Christal Fields, Alrick Hollingsworth, Karisa Morikawa, John Rogers, LaTonya Rogers, and Lynette Todd።ቪዥአል አርት የተሰራው በ Maketa Wilborn እና በ Mari Shibuya ነው።

**ስለዚህ መመሪያ** አስተያየት እና ጥያቄ ካሉት እባክዎ የሚከተለውን ድህረገጽ ይጎብኙ zydinfo@kingcounty.gov. ስለ ዜሮ ዩዝ ዲቴንሽን ለማወቅ ከፈልጉ zeroyouthdetention.com በመሄድ መረጃን ማግኘት ይችላሉ።